# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂውማኒቲስ፣ቋንቋዎች ጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ስነጹሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ

## ትምህርት የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

**በሲዳምኛ አፍ ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ሰዋስዋዊ ስህተቶች ትንተና በአዳሬ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት**


በ

መስከረም በየነ


ጥቅምት 2016

አዲስ አበባ

# በሲዳምኛ አፍ ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ሰዋስዋዊ ስህተቶች ትንተና በአዳሬ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

ለተግባራዊ ሥነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

መስከረም በየነ

ጥቅምት 2016

አዲስ አበባ

## መታሰቢያነቱ

ስለሀገራቸው ክብር ሲሉ ሕይወታቸውን መስዕዋት ላደረጉ ለሀገር መከላከያ ሰራዊትና በየቦታው ለተፈናቀሉ ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ይሁንልኝ፡፡

## አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ

## የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጋዜጠኝነት እና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

## በሲዳምኛ አፍ ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ሰዋስዋዊ ስህተቶች ትንተና በአዳሬ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

### የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | | |
|---|---|---|
| ______________ | ______________ | ______________ |
| አማካሪ | ፊርማ | ቀን |
| ______________ | ______________ | ______________ |
| ፈታኝ | ፊርማ | ቀን |
| ______________ | ______________ | ______________ |
| ፈታኝ | ፊርማ | ቀን |

# ምስጋና

በቅድሚያ ከሁሉ በላይ የሆነው ሁላችንንም የሚያኖረን ትምህርቱንና ጥናቴን ስሠራ ጤናና ዕድሜ ሰጥቶኝ ምንም ችግር ሳይኖር ለዚህ ያደረሰኝ እግዚብሄር ይክበር ይመስገን፡፡

በመቀጠል የድህረ ምረቃት ትምህርቴን ጀምሬ እስካጠናቅቅ ድረስ ያስተማሩኝን የአማርኛ ቋንቋ ት ም ህ ር ት ክፍል መምህራን እና የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን ላመሰግን እወዳለሁ፡፡

ከሁሉም አብልጬ የላቀ ምስጋና የማቀርበው ውድ ጊዜያቸውን ለእኔ አሳልፈው ሰጥተው በእውቅ ክህሎታቸውና ልምዳቸው መምህሬ እና አማካሪዬ ለሆኑት ፕሮፌሰር ጌታሁን አማረ ያለመሰልቸት ስህተቶቼን እያረሙ፣ እያበረታቱ እና ተስፋ እየሰጡ ለዚህ ውጤት በማብቃታቸው ከፍ ያለ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

እናት አባቴን፣ እህት ወንድሞቼን እና መላው ቤተሰቦቼን ትምህርቴን ተምሬ እዳጠናቅቅ የሞራል ስንቅ በመሆን እንዲሁም ያላቹን ነገር ያለምንም መሠሠት ስለለገሳችሁኝ፣ አራአያም ጭምር ስለሆናችሁኝ ውድ ቤተሰቦቼ ከልብ አመሰግናችኋለሁ፡፡

የእኔን መማር እንደራሱ በመቁጠር እኔ ስማርም ሆነ ይህን ጥናት ስሰራ ነጻ እንድሆን ልጆቻችንን በመንከባከብ እንደ ወንድም፣እናትና አባት በመሆን ከጎኔ የሆነውን ውድ ባለቤቴን አየነው አመሰግነዋለሁ፡፡በመቀጠልም እኔ ስማር እና ይህን ጥናት ስሰራ የእናትነትን ፍቅር በወጉ ሳያገኙ እነርሱም ሳያስቸግሩኝ በትዕግስት ላስጨረሱኝ ውድ ልጆቼ አብሳላት አየነውና በአምላክ አየነውን አመሠግናለሁ፡፡

በመጨረሻም ለዚህ ጥናት ግብዓት የሚሆኑትን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ስሰበስብ የዚህ ጥናት ባለድርሻ አካላት ለሆናችሁ የአዳሬ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች፣ የስራ ሀላፊዎች እና ባልደረቦቼ አመሠግናችኋለሁ፡፡

# ማውጫ


| ማውጫ | ቁጥር |
|---|---|
| ምስጋና | i |
| ማውጫ | ii |
| አጠቃሎ | iv |
| ምዕራፍ አንድ | 1 |
| 1.መግቢያ | 1 |
| 1.1.የጥናቱ ዳራ | 1 |
| 1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት | 2 |
| 1.3.የጥናቱ ዓላማ | 3 |
| 1.4.የጥናቱ ጠቀሜታ | 3 |
| 1.5.የጥናቱ ወሰን | 3 |
| ምዕራፍ ሁለት | 4 |
| 2. ክለሳ ድርሳናት | 4 |
| 2.1.የሰዋስው ምንነት | 4 |
| 2.1.1.የሰዋስው ሚና በቋንቋ አጠቃቀም ውስጥ | 4 |
| 2.2.የጽህፈት ክሂል ምንነት | 5 |
| 2.2.1.የጽህፈት ትምህርት ዓላማ | 5 |
| 2.2.2.የጽህፈት ክሂል አቀራረብ | 6 |
| 2.2.3.መጻፍ ለምን አዳጋች ይሆናል | 6 |
| 2.3.የስህተት ምንነት | 8 |
| 2.4.የስህተት ትንተና አስፈላጊነት | 8 |
| 2.5. የስህተት ምንጮች | 9 |
| 2.5.1.የአፍ መፍቻ ተፅዕኖ | 9 |
| 2.5.2.የውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ | 10 |
| 2.5.3.የክፍል ጊዜ ማነስ | 10 |
| 2.5.4.ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች | 10 |
| 2.6. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት | 11 |
| ምዕራፍ ሶስት | 14 |
| 3.የጥናቱ ዘዴ | 14 |

3.1.የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ.....14
3.2.የተማሪዎች ናሙና አወሳሰድ.....14
3.3.የመምህራን ናሙና አመራረጥ.....15
3.4.የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች.....15
3.4.1.በተማሪዎች የሚጻፍ ድርሰት.....16
3.4.2.የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ.....17
3.4.3.የመምህራን ቃለመጠይቅ.....17
3.5.የመረጃ አጠነቃቀርና አተናተን.....17
3.5.1.በተጠኚ ተማሪዎች የተጻፉ ድርሰቶች ትንተና.....17
3.5.2.የመጠይቆች ትንተና.....18
ምራፍ አራት.....19
4.የጥናቱ ውጤት ትንተና.....19
4.1.በድርሰቶቹ ውስጥ የተስተዋሉ አጠቃላይ የስህተቶች ዓይነት እና ብዛት.....19
4.2.ዋናዋና የስህተት ዓይነቶች ምድቦች.....20
4.2.1.የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት.....21
4.2.2..የቋንቋ አወቃቀር ስህተት.....31
4.3.መመደብ ያልተቻሉ ስህተቶች.....37
ምዕራፍ አምስት.....52
5.ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳብ.....52
5.1.ማጠቃለያ.....52
5.2.የመፍትሄ ሀሳብ.....53
ዋቢ ጽሁፎች.....54
አባሪዎች.....58

# አጠቃሎ

*ይህ ጥናት ዋና አላማ አድርጎ የተነሳው በሲዳማ ክልል በሀዋሳ ከተማ አዳሬ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አፋቸውን በሲዳምኛ ቋንቋ  የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ሰዋስዋዊ ስህተቶች መለየት ነው፡፡ ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ የሚከተሉት የዓላማ ጥያቄዎች፣ የሚሉትን ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት በታላሚ ተማሪዎች በተጻፉ ድርሰቶች እና የጽሁፍ መጠይቆች እንዲሁም ከአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር በተደረጉ የቃለመጠይቅ ምልልሶች መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል፡፡ በድርሰቶቹ ውስጥ የተስተዋሉ አጠቃላይ የስህተቶች ዓይነት እና ብዛት የተቆጠሩት በሁለት ዙር በተጻፉት 240 ድርሰቶች ውስጥ ነው፡፡ ታላሚ ተማሪዎች ሁለቱን ድርሰት ለመጻፍ የተጠቀሙባቸው ቃላት ብዛት በአማካይ 92.8 ሲሆን በአንድ ድርሰት በአማካይ የተገኘው ስህተት 33.32 እና የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 36 ነው፡፡ በጥናቱ የታዩ መሠረታዊ የስህተት ዓይነቶቹ የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች፣ የቋንቋ አወቃቀር ስህተቶቸ እና ምድብ የሌላቸው ስህተቶች በዋናነት ተለይተዋል፡፡ ከነዚህ ስህተቶቸ በተጨማሪ በተማሪዎች የተሞሉ የጽሁፍ መጠይቆች እና የመምህራን ቃለመጠይቅ ምልልስ በድጋፍ ሰጪ መረጃነት ተተንትኗል፡፡ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ለሰዋስዋዊ ስህተቱ መንስዔ የሆኑት በመረጃዎቹ ትንታኔ መሠረት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንደሆነ ፣የሲዳምኛ እና የአማርኛ ቋንቋ አናባቢ እና ተናባቢ ሆሄያት (ድምጾች) ልዩነት እና የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሥርዓተ-ጽህፈት ወይም መዋቅራዊ ህግ ጭምር መሆኑ ተደርሶበታል፤በተጨማሪ የመማር ማስተማሩ ሂደት፣ የማስታሪያ ግብዓቶች፣ማህበራዊ እና ሥነልቦናዊ ሁኔታዎች በቀጥታ  የስህተት ምንጭ ወይም መንስዔ ባይሆኑም ለአፈጻጸሙ መንገድ ከፍተዋል፤ እነዚህን ችግሮች (ስህተቶች) ከነመንስዔያቸው ለማስወገድ በአፍመፍቻ ቋንቋቸው እና በአማርኛ ቋንቋ መካከል ያለውን የአናባቢ እና ተናባቢ ድምጾች (ሆሄዎች መካከል) ያለውን ልዩነት ከዝቅተኛ ክፍል ጀምሮ ማለማመድ፣በሲዳሚኛ እና በአማርኛ ቋንቋ መካከል ያለውን የመዋቅር ህጎችን ተማሪዎቹ እንዲለዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንደሚያስፈልግ ጥናቱ ጠቁሟል፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

# 1.መግቢያ

## 1.1.የጥናቱ ዳራ

ስለ ቋንቋ ምንነት ጌታሁን፣(1990:iv) ሲያብራሩ ቋንቋ የሰው ልጅ ከሌሎች እንስሳት የሚለይበት ፀጋው በመሆኑ ከሰው ልጅ ጋር ጥብቅ ትስስር ያለውና የእለት ተእለት መግባቢያው ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

በተመሳሳይ ጌታቸው፣(2011፡xi) "ቋንቋ፤የሰው ልጅ ለሚሠራቸው ነገሮች ሁሉ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ የሰውን ልጅም በምድር ላይ ከሚኖሩት እንስሳት ሁሉ የለየው መሠረታዊው ነገር ቋንቋ ነው፡፡ ምክንያቱም ያለቋንቋ ሰው በለተ ዕለተ ሕይወቱ አንዳችም ነገር ለማድረግ በእጅጉ ስለሚሳነው ነው" በማለት ገልጸውታል፡፡

አማርኛ በሁለተኛ ደረጃ ትምህር ቤቶች በትምህርትነት ከሚሰጥባቸው አጠቃላይ ዓላማዎች ውስጥ አንዱ ተማሪው የቋንቋውን ሥርዓት ጠብቆ ሀሳቡን በጽሑፍ መግለጽ የሚቻል እንዲሆን ማስቻል መሆኑን የአምላክ ሥራ፣ (2008) ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም ጽሕፈት ማህበረሰቡ በዘፈቀደ በተስማማባቸው ትዕምርቶች ወይም ፊደላት ተቀርፀው በመጻፍያ ቁስ ላይ ወይም በማንኛውም ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ነገር ላይ ሀሳብን በማስፈር መልዕክት ሂደት ነው፡፡ የፅሕፈት ክሂል እንደ ሌሎቹ ክሂሎች በመደበኛው ትምህርት ቤት በመማር የሚገኝ ክሂል ነው፡፡ በተመሳሳይም አንድን ቋንቋ በመልመድና በመጠቀም ሂደት ካሉት ክሂሎች ውስጥ ጽህፈት በትምህርት ብቻ የሚገኝ ክሂል እንደሆነም Park (2004) ገልፀውታል፡፡

በተጨማሪ Ellis (2009) መጻፍን ሲገልጹ፣የአንድ ቋንቋ ድምፆች በሚወክሏቸው ምልክቶች አማካኝነት ወረቀት ላይ የሚሰፍሩበት እና መልዕክት የሚተላለፍበት ክሂል ነው፤በማለት እኚሁ ምሁር ፅሑፉ ለበርካታ ተማሪዎች ፈታኝ ነው ብለዋል፡፡

የላይኞቹን ሀሳብ በመደገፍ Norrish (1992) እንደገለጹት ፀሐፊው የሚያስተላልፈው መልዕክት ለተቀባዩ ግልፅ እንዲሆንለት አሻሚ የሆኑ ጉዳዮች እንዲቀንሱለት ፀሐፊው ከፅህፈት በፊት በጥንቃቄ የተሞላ ቅድመ ዝግጅት እና በቂ ልምምድ እንደሚያስፈልገው ገልፀዋል፡፡

የቋንቋ ትምህርት ሲሰጥ የቋንቋ ክሂሎችንም ሆነ ዕውቀቶችን ዓላማው አድርጎ ተማሪዎች በሰዋስው ዕውቀት ላይ የተመሠረተ ተግባቦትን ማበልጸግ እንደሆነ በአማርኛ መማሪያ መጽሀፎች ላይ ተገልጽዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ሰዋስው የቋንቋ ሥርዓት መሆኑን (ባየ 2000) "የአንድን ቋንቋ ስርዓት ከድምጽ አሰካኩ እስከ ሀረግ አመሰራረቱ ድረስ የሚያሳይ ሳይንስ ነው፡፡" በመሆኑም ሰዋስው የሚለው ጽንሰ ሀሳብ የሚገልጸው በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉትን የድምጾችን፣የቃላትንና የሀረጋትን ስርዓታዊ ስደራ የሚመለከት ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሑፍ በሚገባ አቀናብረው ለመፃፍ በርካታ ተግዳሮቶች ያሉባቸው መሆኑን በበርካታ ጥናቶች ታይቷል፡፡ የተማሪዎች የድርሰት አፃፃፍ ስህተቶችን መሰረት (2003) በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች የሚመደቡ መሆናቸውን ሲገልጹ የብቃት ስህተትና የችሎታ ስህተቶች ናቸው በማለት ያብራሩዋቸዋል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ጽህፈት በቋንቋ ውስጥ ድምጾችን የሚወክሉ ትዕምርቶችን ከመለየት አንስቶ በማቀናጀት አረፍተ ነገር ስደራ ድረስ ያለ ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም የሰዋስው፣የአገባብና የቃላት አመራረጥ እንዲሁም የሥርዓተ ነጥቦችን አጠቃቀም ብቃት የሚጠይቅ ክሂል ነው፡፡ ስለሆነም ይህን ብቃት ለማምጣት የግድ መማርን ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ጽሁፍ መረጃዎችን ማስተላለፊያ ክሂል እንደመሆኑ፣ሆሄያትን በመልካቸው የማስቀመጥ፣ቃላትን ከሚኖራቸው ትርጉም አንጻር የመጠቀም፣አንቀጾችን ሥርዓት ባለው መልኩ የማዋቀር፣አረፍተነገሮችን በወጉ አዋቅሮ ተገቢ የሆነውን መልዕክት እንዲያስተላልፉ በማድረግ የመጠቀም ችሎታቸውን ይጠይቃል (Kavaliauskiene, 2009)፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረት በሲዳማ ክልል በሀዋሳ ከተማ አዳሬ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አፋቸውን በሲዳምኛ ቋንቋ የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ሰዋስዋዊ ስህተቶች መለየት ነው፡፡ በመሆኑም አማርኛ ኢ-አፍ ፈት የሆኑ የሲዳምኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ በተደጋጋሚ የሚፈጽሟቸውን ሰዋስዋዊ ስህተቶች በመመልከቱ የሚሳሳቱትን ስህተትና የመሳሳታቸውን ምክንያት በመለየት መፍትሄ ለመሻት ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት በተመረጠው ት/ቤት በሲዳምኛ አፈ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ሰዋስዋዊ ስህተቶች ለመለየትና ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ለመመርመር የሚከናወን ይሆናል፡፡

## 1.3.የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሲዳማ ክልል በሀዋሳ ከተማ አዳሬ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አፋቸውን በሲዳምኛ ቋንቋ  የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ  ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ሰዋስዋዊ ስህተቶች መለየት ነው። ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች በጥናቱ ምላሽ ያገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል።

- በሲዳምኛ ቋንቋ  አፍ ፈት የሆኑ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ  ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን የሰዋስዋዊ ስህተቶችን ዓይነት መለየት።
- ተጠኚዎቹ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ  ደርሰት ሲጽፉ ከሚፈጽሟቸው ሰውስዋዊ ስህተቶች ውስጥ የትኛው ስህተት በብዛት እንደሚደጋገም መለየት ።
- ለሰዋስዋዊ ስህተቶቹ የመከሰት ምንጭ(መንስኤ) ምን ምን እንደሆነ መፈተሽ ናቸው።

## 1.4.የጥናቱ ጠቀሜታ

በዚህ ጥናት በሲዳምኛ ቋንቋ አፍ ፈት የሆኑ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ሰዋስዋዊ ስህተቶች ለመለየት በመሆኑ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል።

- ታላሚዎቹን ተማሪዎች መምህራን በአማርኛ ድርሰት በሚያጽፉቸው ጊዜ የሚከሰቱ ችግሮችን በመለየት እንዲፈቱ ያግዛል።
- በመማር ማስተማሩ ሂደት የአማርኛ ቋንቋን የጽህፈት ሥርዓት ለይቶ በማወቅ ለተግባቦት ለመጠቀም ይረዳል።

❖ መምህራን ተማሪዎቹን ድርሰት አጽፈው ሲያርሙ የተከሰተውን ሰዋስዋዊ ስህተት ምንጭ በማወቅና በመለየት ምጋቤ ምልሽ ለመስጠት ያገለግላል።

- ከዚህ ርዕስ ጋር ተመሳሳይነት ወይም ተዛማጅነት ያለውን ጥናት ለሚያጠኑ የትምህርት ባለሙያዎች በመነሻነትና በተዛማጅ መረጃነት ሊያገለግል ይችላል።

## 1.5.የጥናቱ ወሰን

የጥናቱ ትኩረት በተመረጠው ትምህርት ቤት በሲዳምኛ ቋንቋ  አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ  ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ሰዋስዋዊ ስህተቶች ለመለየት የሚካሄድ  ነው። ከይዘት አኳያ ታላሚዎች ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ  ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ፍተሻ  ላይ የሚያተኩረ ሲሆን የስህተቱንም ምንጭ ይለያል።

## ምዕራፍ ሁለት

# 2. ክለሳ ድርሳናት እና

## 2.1.የሰዋስው ምንነት

ስዋስው የቋንቋ ሥርዓት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህን ሥርዓት መሠረት ከሚያደርጋቸው ተዋቃሪዎች ረገድ የተግባቦት ልዩነት ይታያሉ፡፡ በዚህም መሰረት ብዙዎቹ ብያኔዎች ሰዋስው፣ ዓረፍተ ነገሮችንና የቃላትን የቅንጅት ሥርዓት የሚመለከት፣በዓረፍተ ነገር ደረጃ የሚታይና የቋንቋውን ተናጋሪዎች ስምምነት መሠረት ያደረገ ቅደምተከተላዊ መሆኑን (Brown, 1994:45) ይገልጻሉ፡፡

በተጨማሪ Ur,(1996፡32) እንደገለጹት "ሰዋስው በዓረፍተ ነገር ደረጃ ብቻ የማይገደብ እና በቃልና በሀረግ ደረጃም የሚታይ ሥርዓታዊ አገባባ ነው፡፡ የአገባብ ሥርዓቱ ደግሞ ድምጾች ምዕላድን ወይም ቃላትን ለመመስረት ከሚፈጥሩት ቅንጅት የሚጀምርና እስከ ዓረፍተ ነገር ምስረታ የሚዘልቅ ነው፡፡"

ስለሰዋስው ምንነት ባየ (2003፡13)"ቀደም ባለ ጊዜ ስለሰዋስው የነበረ ግንዛቤ በሀረግና በዓረፍርተ ነገር አመሰራረት፣አይነትና አገባብ ላይ ብቻ ስለሚያተኮር ውሱን ነበር ነበር፤በድምጽ አፈጣጠርና በቃላት አመሰራረትም ላይ የነበረው ትኩረት ዝቅተኛ ነበር፡፡ ከድምጽና ከቃላት ባህሪ ይልቅ በፊደልና በመዝገበ ቃላት አዘገጃጀት እንዲሁም በአገባብና በትርጉም ላይ መጠነኛ ትኩረት ነበረው፡፡"

በአጠቃላይ እነዚህን ሀሳብ ጠቅለል ባለመልኩ ሲገለጽ ሰዋሰው ከቋንቋ ጥናት ውስጥ ስርዓትን የሚመለከት ክፍል ሲሆን፣ የሰዋሰው መኖር አንድን ቋንቋ የተሟላ የቋንቋ ተግባር እንዲፈፅም የሚያደርግ እና ተገቢውን የቋንቋውን አገልግሎት እንዲሰጥ ዋና ድርሻ ያለው ነው ማለት ይቻላል፡፡

### 2.1.1.የሰዋሰው ሚና በቋንቋ አጠቃቀም ውስጥ

የሰዋስው ሚና የምንለው በአረፍተነገር መዋቅር የሚገኙት ተዋቃሪዎች በተገለጸው ድርጊት ውስጥ ድርጊት ፈጻሚነት፣ድርጊት ተቀባይነትን እና ድርጊቱ እንዲፈጸም ያደረገውን የሚገልጹ ናቸው፡፡ በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ የእነዚህ መኖርና አለመኖር የሰዋስውን ሚና ከፍ ወይም ዝቅ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ የሰዋስውን ሚና ከፍና ዝቅ ሊያደርጉ የሚችሉ ተዋቃሪዎች የሚባሉት የአረፍተ ነገር ባለቤት፣ተሳቢ፣ አጎላማሽ (መሙሊያዎችና) ግሶች

ናቸው። በአረፍተ ነገር ውስጥ የተዋቃሪዎች ቁጥር ሲጨምር የሰዋስው መዋቅር ከፍ ይላል ሲቀንስ ደግሞ መዋቅሩ ዝቅ ይላል ማለት ነው (Ur, 1996) ።

ይህ አገላለጽ በሰዋስው የቋንቋ ትምህርትን ክህሎት ከማሳደግ ባሻገር ተማሪዎች ሊገነዘቡ የሚገባቸውን የተግባቦት ዕውቀት ማስፋት ይኖርባቸዋል። የሰዋስው ሚና በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከፍተኛ አገልግሎት እንዳለውና ቋንቋውን በአግባቡ ለመጠቀም ከቋንቋው ተጠቃሚ በሚጠበቀው ሁኔታ ስርአቱን ማወቅ በተግባቦት ጊዜ ለመጠቀም የሚያስችል በቂ ችሎታ ሊኖረው እንደሚገባ ነው የሰዋሰው እውቀት መኖር የቋንቋ መዋቅር እና የአጠቃቀም ሚናውን እንደሚያሳድግ ነው የተገለጸው።

## 2.2.የጽህፈት ክሂል ምንነት

በቋንቋ ተግባቦት ሂደት መሠረታዊ ከሚባሉት አራቱ ክሂሎች አንዱ መጻፍ ሲሆን ለሀሳብ ማስተላለፊያነት የሚያገለግል ነው። መጻፍ፣የተለያዩ ጽሁፋዊ ክንውኖች የመጨረሻ ውጤት የሆነ የሀሳብ ማስተላለፊያ ነው፤በመሆኑም መጻፍ የድምጽ ወኪል በሆኑ ትዕምርቶችና ምልክቶች አማካኝነት የሚተገበር የመልዕክት ማስተላለፊያ ነው። የመጻፍ ክሂል ከንግግር ክሂል በመቀጠል የመጣ ቢሆንም ለሰው ልጆች የሚሰጠው ጥቅም ከፍ ያለ ሲሆን በዋናነት ዕውቀት የሚቀሰምበትና የሚተላለፍበት፣ታሪክ የሚመዘገብበትና ከዘመን ወደዘመን የሚሸጋገርበት ድልድይም ነው (Tangerpermpoon, 2009)።

ከዚህ ገለጻ የምንረዳው ጽህፈት ሆሄያትን በማቀናጀት ቃላትን እና ዓረፍተ ነገር በመመስረት የራስን ሀሳብ ወይም መልዕክት ለሌሎች የሚተላለፍበት መንገድ ነው፤በመሆኑም መጻፍ ንግግር በወረቀት የሚወከልበት ለትውልድ መተላለፍ ያለበት ቅርስም ሆነ ዕውቀት ከትውልድ ወደ ትውልድ ማሸጋገሪያ የተግባቦት አንዱ ዘርፍ ነው።

በተጨማሪ ስለመጻፍ ክሂል Byrne (1988) እንደ ገለጹት “አንባቢው ሊረዳው በሚችል መልኩ ለድምጾች ውክልና በተሰጣቸው ትዕምርቶች አማካይነት ሀሳብን መግለጽ መቻል ነው። በማለት ገጸዋል።

### 2.2.1.የጽህፈት ትምህርት ዓላማ

የጽህፈት ትምህርት ተቀዳሚ አላማ ተማሪዎች በጽሁፍ አማካኝነት ሀሳባቸውን በተቃና መንገድ በመግለጽ ጽሁፋዊ ተግባቦትን እንዲለማመዱ ማስቻል እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ። Raimes (1983፡4-7) ተማሪዎች ጽህፈትን የሚማሩባቸው ዓላማዎች ዓረፍተ ነገሮችን ከመጻፍ በዘለለ መልኩ ሊታዩ ይገባቸዋል በማለት በገለጻዎቹ የሚያካትቷቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ይዘረዝራሉ። እነሱም ከአንባቢ ጋር ለመግባባት እና ከገጽ ለገጽ

ተረክበውም ሃሳብን በጽሁፍ ለመግለጽ፣ዕውቀትን ለማግኘት፣ ከእለት ተዕለት የህይወት ገጠመኞች የሚታዩ ክስተቶችን መዝግቦ ለማቆየት እና በቋንቋው የሚጻፍ የጽሁፍ ሥራዎች በተማሪዎች እንግዳ እንዳይሆኑ ማስቻል ናቸው በማለት ገልጸዋል ፡፡

ከዚህ ገለጻ የምንረዳው ነገር በኖር የጽህፈትን ዓላማ ከግለሰባዊና ማህበራዊ ጠቀሜታው አንፃር ሲታይ ጽህፈትን መማር ለግለሰቡ ሀሳቡን ከመግለጽ ያለፈ ዕውቀትን ለመቅሰም፣አዕምሯዊ ተግባራትን ለማከናወንና የተጻፉ ጽሁፎችን ለመጠቀም ለማህበረሰቡም የጽሁፍ ቋንቋ ቅርስ ለመስያዝ እና የሥነ-ጽሁፍ ሥራዎችን ልዩ ልዩ መረጃዎችን ለማጠናከር ያገለግላል፡፡

እንደ Heaton (1991:138) አገላለጽ ጽህፈትን መማር የተለያዩ የጽህፈት ንዑሳን ክሂሎችን (ዓረፍተ ነገሮችን የመጻፍ፣ተቀባይነት ያለውን አስተሳሰብ የመምረጥ፣የማፍለቅና የማቅረብ ፣ተፈላጊውን መልዕክት ለማስተላለፍ ሥርዓታዊ የአጻጻፍ ስልቶችን የመምረጥ፣የዓረፍተ ነገርና አንቀጽ አወቃቀር ሥርዓትን ጠብቆ የመጻፍ፣የተለመደና መደበኛ ቋንቋን የመጠቀም ወዘተ.) ለማዳበር እንደሚቻል አብራርተዋል፡፡

### 2.2.2.የጽህፈት ክሂል አቀራረብ

ቀድሞ በነበረው ትምህርት ውስጥ ጽህፈት እንደ ሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ትርጉም ትኩረት አግኝቶ የቆየ ሳይሆን ሰዋስውን ለማስተማር ካለው ጠቀሜታ አንጻር ብቻ የሚታይ እንደነበር ነው (Richard, 1990)፡፡

ይህ አባባል ሰዋስውን ለመማርም ሆነ ለማስተማር የጽህፈት ሥርዓት አስፈላጊ እንደሆነ ነው፡፡ በመሆኑም ለመጻፍ ሲታሰብ የሰዋስው ሥርዓት እንደሚታሰብ ነው፡፡

ነገር ግን ዛሬ ጽህፈት በየትኛውም የቋንቋ ትምህርት ውስጥ ይሰጣል፤የመጻፍ ክሂል ካለው ፈታኝ ባህሪ አኳያም በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በተማሪዎች የሚፈጸሙ በርካታ ስህተቶች መኖራቸውን አክለው በመገልጽ ችግሮቹን ለመለየት እና ለመፍታት የሚደረጉ ጥናቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ መሄዳቸውን አስረድተዋል (Park, 2004)፡፡

### 2.2.3.መጻፍ ለምን አዳጋች ይሆናል

መጻፍ የሀሳብ አቀነባበርንና ፍሰትን፣የቃላት አመራረጥንና የአገላለጽ ስልትን የሚጠይቅ የቋንቋ ክሂል ነው፡፡ በመሆኑም ብዙዎች እንደሚስማሙበት መጻፍ ከሂሊና ሀሳብን የማፍለቅና ለሰዎች የማስተላለፊያ መንገድ መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡ ሆኖም ግን አስቸጋሪ እንደሆነም ያስቡታል፡፡ መጻፍ ለብዙዎች አስቸጋሪ የሚሆንበትን ምክንያት

Byme, (1988) ሲያስረዱ ሦስት ምክንያቶች እንዳሉ ነው እንሱም የሥነ-ልቦና ዝግጅት ችግር፣ሰዋስዋዊ ችግርና ግንዛቢያዊ ችግር ሲሆኑ በአጭሩ እንደሚከተለው ይዘረዘራሉ፡፡

- የሥነልቦና ዝግጅት ችግር፡- መጻፍ ከንግግር የበለጠ ሥነልቦናዊ ጫና ያሳድራል፡፡ Byme (1997:4) ሲያብራሩ ንግግር ተፈጠሯዊ በየትኛውም ስፍራ እና አጋጣሚ የምንጠቀመው የመግባቢያ መንገድ ነው፡፡ በየትኛውም ሁኔታ ስንናገር ብንሳሳት ከታዳሚ እርማት እንሰጣለን፤አመለካከታችንን በጽሀፈት ስንገልጽ ግን ያለማንም እገዛና ማስተካከያ በራሳችን የምንወጣው ሂደት ይሆናል፡፡ ይህ ሁኔታ የሥነልቦና ጫና ስለሚፈጥር መጻፍን አስቸጋሪ ያድገዋል፡፡
- ሰዋስዋዊ ችግር፡- በአንድ ጉዳይ ላይ ገለጻ ስናደርግ አድማጭ ንግግራችን እንዳይደናቀፍ ይረዳናል፡፡ ንግግር ላይ ችግር ቢከሰት ወደፊትና ወደኋላ እያልን ማስተካከል እንችላለን፡፡ በጽህፈት ጊዜ ግን እንደንግግር ማድረግ አንችልም፡፡ተግባቦታችን በራሳችን ችሎታና ዕውቀት የተገደበ ይሆናል፡፡ በራሳችን የቃላት ምርጫ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት ይጠበቅብናል፡፡ ከዚህ ሂደት በኋላ ነው ጽሁፋችን በአንባቢ የሚተረጎመው፡፡ ይህ ደግም ጽህፈትን አስቸጋሪ ያደርገዋል (Byme, 1997:4-5)
- የግንዛቤ ችግር፡- በዚህም ጊዜ ንግግር መልዕክት ለማስተላለፍ ያለማንም ረዳትነት በራሳችን ፍላጎት በፈለግነው ጊዜ የምንጠቀመው መግባቢያ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ምንም ዓይነት ትምህርት አያስፈልግም፤መጻፍ ግን የራሱ ህግና ሥርዓት ያለው መግባቢያ ነው፡፡ የቋንቋውን የጽህፈት ሥርዓት ብቻ ሳይሆን ማወቅ ያለብን ሀሳባችንን በጽሁፍ አፍልቀን ከአንባቢ ጋር እንዴት መግባባት እንደምንችል ማወቅ ይጠበቅብናል፡፡ እኔ ሶስተኛው መጻፍን አስቸጋሪ የሚያደርገው ሂደት ነው በማለት ገልጸዋል (Byme, 1997:5)፡፡

ከላይ ስለመጻፍ አስቸጋሪነት የተገለጹት እና የተዘረዘሩት ሀሳቦች መጻፍ የተለያዩ የሀሳብ ቅንብሮችን ለአንባቢ የማስተላለፍ ሂደት ቢሆንም የሰዋስው አጠቃቀም፣የሥነልቦናና የግንዛቤ ችግር እነደሚኖር ነው፡፡

ስናጠቃልለው የጽህፈት ክሂል ድምጾችን በሚወክሉ ሆሄያት መልዕክትን ወይም ሀሳባችንን ለተደራሲ የምናስተላልፍበት ክሂል ነው፡፡ በጽሁፍ የምናስተላልፈው መልዕክት ከአንባቢው ጋር ሊያግባባን የሚችለው የታላሚውን ቋንቋ ሥርዓት አስተካክለን ወይም አውቀን ከጻፍን ብቻ ነው፡፡ይህን ሥርዓት ለማወቅ ደግሞ መማር እና መለማመድ ያስፈልጋል፡፡ ጽህፈት ከተግባር ጋር ግንኙነት ስላለው ዘውትር በሚደረጉ ልምምዶች ይሻሻላል፣

ይዳብራል፤በመሆኑም ተለማማጁን ጥሩ ጸሀፊ ያደርገዋል፡፡

## 2.3.የስህተት ምንነት

አንዳንድ የቋንቋ ምሁራን በስህተት ምንነት ላይ ጥናቶችን አጥንተዋል፡፡ ለአብነት ያህል ከዚህ በታች ጥቂቶቹን እንገልጻለን፡፡

ስህተት በማንኛውም ሰው ጊዜና ቦታ ሳይመርጥ የሚፈጽመው አፍ-ፈትና ኢ-አፍፈት የማይል ሲሆን አፍ ፈት ተናጋሪዎች መሳሳታቸውን ተረድተው ግድፈቱን ወዲያውኑ ሊያርሙት ይችላሉ፡፡ ይህም አፍ ፈቶች ችሎታ ወይም ብቃት ማነስ የሚፈጸም ሳይሆን በአፍልቆት ሂደት የተወሰነ ክፍተት መኖሩንና ክፍተቱም ከዘፈቀዳዊ የቋንቋ አጠቃቀም፣ ከአፍ ማዳጥ፣ ከጭንቀትና በመሳሰሉት ምክንያቶች ሊከሰት የሚችል ነው፡፡ ስህተት የምንለው ፅንሰ ሀሳብ ግን የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችን ከታላሚው ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርአት አፈንግጠው የሚፈጽሙት ወይም የሚናገሩት ሲሆን የተማሪዎችንም ቋንቋ ብቃት የሚያንፀባርቅ መሆኑን ገልጿል (Brown, 1998)፡፡

በተጨማሪም ተክሌ (1989) በፃፉት ጥናታዊ ጽሁፋቸው ስህተቶች በተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ የሚፈጠሩ በህብረተሰቡ ዘንድ ያልተለመዱ ክንዋኔዎች ናቸው፡፡ ይህ በአጠቃላይ ሲታይ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ቋንቋን ከመማር ሂደት አኳያ ሲታዩ ስህተቶች የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ ይላሉ፡፡ በጥቅሉ በቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ የሚጸሙ ስህተቶች በትምህርት የሚቀርበው ቋንቋ ወይም የተማሪው አፍ መፍቻ ቋንቋ ከሚያስከትለው ተፅዕኖ የሚሰርፁ ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡ በዚህ ሁኔታ የትኛውንም ቋንቋ በአፍ መፍቻነት ወይም በሁለተኛ ሶስተኛ ቋንቋነት ከመደበኛው ትምህርት ውጭ ስንቀስም ወይም በመደበኛው ትምህርት ውስጥ ስንማር ያለስህተት ልንማር እንደማንችል Dulay, (1982)ን እና Corder, (1967)ን በመጥቀስ ተክሌ (1989) በጥናታዊ ጽሑፋቸው አሳይተዋል፡፡

## 2.4.የስህተት ትንተና አስፈላጊነት

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎችን በጽሑፍ ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ልምምድ ያደርጋሉ፡፡ በዚህም ልምምድ ወቅት አፋቸውን በታላሚው ቋንቋ አፍ የፈቱም ሆነ ኢ አፍ ፈት የሆኑ ተማሪዎች የተለያዩ ስህተቶችን ይፈጽማሉ፡፡ ነገር ግን ስህተቶቹ ለተማሪዎቹ የቋንቋ እድገት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ እንጂ የውድቀት ምልክት እንዳልሆኑ የተለያዩ የቋንቋ ምሁራን ይገልጻሉ (Littlwood, 1984)::

Brown (1994) የስህተት ትንተና ማለት የተማሪዎችን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመግለጽ ሲባል በበርካታ ሰዎች ዘንድ ተማሪዎቹ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች የሚታዩበት፣ የታዩት

ስህተቶች የሚተነተኑበት እና የተተነተኑትም የስህተት አይነቶች በተለያዩ ምድብ አይነቶች የሚቀመጡበት ስልት ነው፡፡ ስህተት እንደ አንድ የትምህርት ሂደት ይቆጠራል፡፡ ከዚህም በመነሳት ለስርአተ ትምህርት ቀረፃ፣ ለማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት እንዲሁም ተማሪዎች ያሉበትን የእውቀት ደረጃ ለማመልከት ያግዛል፡፡ በአሰራሩም የቋንቋ ተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም በናሙናነት በመውሰድ ስህተቶችን ለይቶ ያወጣል፣ የስህተቶቹንም አይነት ምንጫቸውንም ሊሆን እንደሚችል መላ ይመታል( Ellis, 1989) (Corder, 1967) (Duley et al, 1982)::

## 2.5. የስህተት ምንጮች

ስለስህተት ትንተና ጥናት ካደረጉት ምሁራን Richards (1971) የተለያየ ዳራ ያላቸውን በተለያዩ ሀገሮች ተማሪዎች ላይ ጥናት አካሂደው በተማሪዎቹ የተፈጸሙ ስህተቶችን ለአብነት የግስንና የአያያዦችን አጠቃቀም ስህተት ጠቁመዋል፡፡

ፅህፈት ብዙ ልምምድን የሚጠይቅ እና በዚህ ልምድ ሂደትም ከድምፆች ቅርጽ እስከ አረፍተ ነገር አወቃቀር ድረስ የተለያዩ ስህተቶች ይፈጠራሉ፡፡ ለሚፈጠሩትም ስህተቶች ደግሞ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የተገመቱ ነጥቦች በተለያዩ ምሁራን የተገለጹ ሲሆን ይህ ጥናትም በብዙ ምሁራን ተዘውትረው የሚጠቀሱ ግምታዊ ሃሳቦችን ለመዳሰስ ይሞክራል፡፡

### 2.5.1.የአፍ መፍቻ ተፅዕኖ

ያምላክ ስራ (2008) እነ Brown (1994)ን ጠቅሰው ሲገልፁ የአፍ መፍቻ ተፅዕኖ የመጀመሪያ ደረጃ መለያ ባህሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሽግግር ወይም  ጣልቃ ገብነት ነው፡፡ ተማሪዎች ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ጋር ከመላመዳቸው በፊት አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሰዋስዋዊ ባህሪ በአእምሯቸው  ተቀርፆ ይገኛል፡፡ እኚህ አጥኚ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪው ፅህፈት ላይ በድምፅ፣ በቃላት፣ በሀረግ እና በዐ.ነገር አወቃቀር ውስጥ ሊታይ የሚችል ቢሆንም ስህተቱ ይበልጥ ጎልቶ የሚታየው ግን በንበት ላይ እንደሆነ አጥኚው በጥናታቸው ገልፀውታል፡፡

በተጨማሪ Norish (1992) ቋንቋን የመማር ሂደት የልምምድ ውጤት በመሆኑ የተማሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ልምድ ጣልቃ በመግባት የስህተት ምንጭ ሊሆን ይችላል፡፡ አዲስ ቋንቋ በምንለምድበት ጊዜ በአዲሱ ልምድ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አሮጌው ልምድ በአዲሱ ልምድ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ምክንያቱም በአንድ ቋንቋ ውስጥ

የምናገኛቸው ድምጾች በሌላኛው ላይ ላናገኛቸው እንችላለን፡፡ እንዲሁም በአንደኛው ላይ የሚናገኘውን የዓረፍተ ነገር መዋቅር በሌላኛውም ላይ ላናገኝ እንችላለን በማለት ገልጸዋል፡፡

ከዚህ አንጻር ማናኛውንም ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተፅዕኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡

### 2.5.2. የውስጠ ቋንቋ ተፅዕኖ

ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ በተለየ ሁኔታ በታላሚው ቋንቋ ውስጣዊ ባህሪ የተነሳ የሚከሰት ስህተት ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የሚፈጠረው ስህተት ተማሪው ታላሚውን ቋንቋ ለመጠቀም ሲፈልግ ለሚያጋጥሙት አዳዲስ ሁነቶች ራሱ ህግ ፈጥሮ ተጠቅም ለማለፍ ሲሞክር የሚፈጠር ወይም የሚከሰት የስህተት ዓይነት ሲሆን በስህተትነት የሚከሰተው የቋንቋ ስርዓት ከአፍ መፍቻም ሆነ ከተተኳሪ ቋንቋ ስርዓት የማይካተት ስለሆነ በቋንቋ መማር ሂደት ተማሪው በመማር የሚያሳየው ለውጥ የተነሳ ፈጥሮ ሲጠቀም የሚከሰት ስህተት ነው (Littlewood, 1984)፡፡

በመቀጠልም Brown (1994) በውስጥ ቋንቋ ተፅዕኖ ሳቢያ የሚፈጠር ስህተት የአፍ መፍቻ ቋንቋን ወይም የታላሚውን ቋንቋ የተከተለ ባለመሆኑ ተማሪው በሁለተኛ ቋንቋ ለመግባባት ሲሞክር ራሱ በሚፈጥረው የቋንቋ ህግ አማካኝነት የሚፈጠር ስህተት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

### 2.5.3.የክፍል ጊዜ ማነስ

በመምህራን የታላሚዎችን ተማሪዎች ስህተት መቀነስ የሚቻለው ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ ሲፅፉ እንዲያስተካክሉ፣ እንዲያርሙ በማድረግ ስህተት  ሙሉ ለሙሉ ባይሆንም በመጠኑ እንዲስተካከል ጊዜ ወሳኝ ነው፡፡ በጊዜ ጉዳይ ላይ (ተስፋዬ 1986) “ከተወሰኑ ዓመታት ወዲህ የተማሪዎች ቁጥር መጨመር እና በትምህርቱ ክፍለጊዜያት ማነስ እየተመካኘ ተማሪዎች የሚጽፉትን ነገር ትክክል ይሁን ስህተት ሳይታረም መቅረቱ በጽሀፈት ላይ ችግር ያስከተለ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ”ከዚህ ገለጻ የምንረዳው በመማር ማስተማር ሂደት ስህተትን ለማረምም ሆነ ለማሳረም በቂ ክፍለ ጊዜ መኖር እንዳለበትና ነገርግን በትምህርት ቤቶች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጠው ክፍለ ጊዜ በቂ እንዳልሆነ ነው፡፡

### 2.5.4.ስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች

ስነ-ልቦናዊ ጉዳይ ሲባል የሚያያዘው ከተማሪዎች ጉዳዮች ጋር ሲሆን ተማሪዎቹ ከክፍል ውጪ ስላለው ሁኔታ በአዕምሮአቸው ውስጥ ይዘውት የሚመጡት ነገር በክፍል ውስጥ

የሚሰጠውን ትምህርት በደንብ እንዳይከታተሉ ስለሚያደርጋቸው ተማሪው ለሚማረው ቋንቋ ያለው በጎ አመለካከት ትምህርቱን በሚገባ እንዲከታተል የማነሳሳቱን ያህል በቋንቋውና በተናጋሪው ማህበረሰብ ላይ ያለው አመለካከት አሉታዊ መሆኑ ደግሞ ለሚማሩት ቋንቋ የሚኖራቸው ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ሁኔታ ከቤተሰቦቻቸው ከአካባቢያቸው፣ ከጓደኞቻቸውና ከተለያዩ ተላውጦዎች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያለው ነው። በዚህም ምክንያት ተማሪዎች ለሚፅፉት ጽሁፍ ያላቸውን ትኩረት ይቀንሳል ስህተቱም በአንጻሩ ይጨምራል (Norrish, 1992:19)::

ከዚህ ገለጻ የምንረዳው ተማሪዎች ለሚማሩት ቋንቋ እና ቋንቋውን ለሚናገሩ ማህበረሰቦች ያላቸው አመለካከት አዎንታዊ ካልሆነ ትምህርቱን በአግባቡ አይከታተሉትም፤ከዚህ የተነሳ ለቋንቋውና ለተናጋሪው ማህበረሰብ ያላቸው አሉታዊ አመለካከት ስህተት እንዲፈጽመ ሊያደርጋቸው ይችላል ማለት ነው።

## 2.6. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያላቸውን ቀደም ጥናቶች በመቃኘት በጥናቶቹ ከተካተቱት ተተኳሪ ነጥቦች የሚከተሉት ተቃኝተዋል። አማርኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶችን በሚመለከት በተለያዩ ጊዜያት በተለያየ ቋንቋና አካባቢ ላይ በርካታ ጥናቶች ተካሄዷል።

ከነዚህ መካከል ደብሬ (1990) በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋናዋና የስህተት ዓይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት አድርገዋል። የጥናቱ ዋና ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶች፣ የስህተት ብዛትና ድግግሞሻቸውን እንዲሁም ዋና ዋና የስህተት ምንጮችን መለየት እንደሆነ አሳይተውናል።

ልዑል ሰገድ (1997) በወላይትኛና ሲዳምኛ ተናጋሪዎች በአማርኛ ድርሰት ውስጥ የታዩ ስህተቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት አቅርበዋል። የጥናቱ ትኩረት በሥነ-ልሳናዊ ስህተቶች ላይ ሲሆን በአራቱ ዋና ዋና ክሂሎች በመከፋፈል ዳስሷቸዋል። የስህተቶቹ ዓይነት በድምጽ፣በቃላት፣በሀረጋት፣እና በዓረፍተ ነገር ውስጥ ከተገኙ ስህተቶች አንጻር የተፈተሹ ናቸው። በተደረገው ጥናት የስህተቶቹ ምንጭ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች፣የማስተማሪያ ዜዴዎች ድክመት እና የሥነልቦና ችግሮች እንደሆኑ ጠቁመዋል።

ዐብይ (1997) ‹‹አዲስ ከተማ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በደብረ ኃይለ ቅዱስ ራጉኤል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ››በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ባካሄዱት ጥናታቸው በተማሪዎች የተፈጸሙ ስህተቶችን ተንትነዋል፡፡ በጥናታቸው የስህተት መንስዔዎችን የመማር ማስተማር ሂደትና ሥነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ላይ ትኩረት ሰጥተዋል፡፡

ምህረት (1998) ‹‹በዋቸሞ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሀዲይኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ትንተና›› በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት አካሄደዋል፡፡ በጥናቱም ትኩረት ያደረጉት የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች፣የቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች እና የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ላይ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በተደረገው ትንታኔ መሰረት ለስህተቶቹ መከሰት በመንስዔነት የተዘረዘሩት የስህተት ምንጮች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ፣የውስጥ ቋንቋ ተፅዕኖ፣የመማር ማስተማር ድክመቶች እና ሥነ-ልቦናዊ ማህበራዊ ሁኔታዎች ተፅዕኖ ናቸው፡፡

ተገኝ (2000)‹‹አፋቸውን በከፍኛ ቋንቋ የፈቱ የቦንጋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሰልጣኝ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና ››በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናታቸው ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉም ሆነ ሲናገሩ የታዩ ስህተቶችን የፊደላት አለቦታቸው መግባት፣ አላስፈላጊ ድግግሞሽ የጾታ አለመስማማት፣ የአያያዦች አለቦታቸው መግባት፣ የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች፣ የቋንቋ አወቃቀር እና የሥርዓ-ተነጥብ አጠቃቀም ችግር በጥናቱ ትኩረት የተደረገባቸው ነገሮች ናቸው፡፡

መሠረት (2003) ‹‹በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች›› በሚል ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት አካሂደዋል፡፡ በጥናታቸው ትኩረት ያደረጉት አብይ ጉዳዮች የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም እና የጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ችግር ናቸው፡፡

ሙልጌታ አብስር (2003) በአርባምንጭ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል አፋቸውን በጋሞኛ ቋንቋ የፈቱ የሁለተኛ ዓመት የክላስተር ዕጩ መምህራን ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና በሚል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ ትኩረት ያደረጉት የጋሞኛ ቋንቋ አፍፊት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶች ፣የስህተት ብዛትና ድግግሞሽ እንዲሁም ዋናዋና የስህተት ምንጮችን መለየት ላይ

ነው፡፡ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ጥናታዊ ጽሑፎች በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን ያልፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ጽሁፋቸው ላይ የተለያዩ ስህተቶች በተገኙባቸው ተማሪዎች ላይ የተደረጉ ፍተሻዎች ናቸው፡፡ የተገኘውን የጥናት ውጤት ስንመለከት ሁሉም ጥናቶች ሰዋስዋዊ ስህተቶች ላይ ትኩረት በማድረግ ለስህተት ምንጭ ይሆናሉ ያሏቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ ከተወሰኑ የመማር ማስተማር ችግሮች ውጪ ለችግሩ መፈጠር ዋና ምክንያት የተባለው የአፍ መፈቻ ቋንቋ እና የውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ነው፡፡ ጥናቶቹ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ዋና ጉዳይ በተጠቀሱት ሁሉም አጥኚዎች ጥናቱ የተካሄደው አማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍፈቶች ላይና በአማርኛ ቋንቋ ጽህፈት በሚጻፉበት ጊዜ በሚፈጠሩ ስህተቶች ላይ የስህተት ትንተና እና ለስህተቱ መፈጠር መንስዔ በሆኑ ነገሮች ላይ ጥናት ማድረጋቸው ሲሆን ጥናቱም መነሻ በመሆን የየበኩላቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች ከዚህኛው ጥናት የሚለዩት የሲዳሚኛ ቋንቋ የሚነገርበት አካባቢ፣ ባህላዊና ማህበራዊ አውድ እንዲሁም በተማሪዎቹ ዳራ ይለያያሉ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3.የጥናቱ ዘዴ

ስለ ምርምር ዘዴ እንደምርምሩ ርዕሱና ዓይነት ያለው (2009፡19) አካሄዱን እንደሚከተለው ይጠቁማሉ፣‹‹እንደመጠናዊ ምርምር ዐይነታዊ ምርምር በተወሰኑ ተለዋዋጮች ላይ የሚያተኩር ሳይሆን ተመራማሪው አንድን ችግር ይወስድና ውስን የሆኑ የችግሩን ባለቤቶች በመምረጥ ያነሳውን ችግር በጥልቀትና በስፋት ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመዳሰስ መረጃዎችን የሚሰበስብበትና የሚተነትንበት ሲሆን ሂደትም የጠነከረና የዳበረ ሳይንሳዊ ሂደትን አይከተልም፡፡ተመራማሪው ከልምዱ በመነሳት መረጃ ይኖራቸዋል ብሎ የሚገምታቸውን ሰዎች በመምረጥ በጥናቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡››

የዚህ ጥና ዓላማ በሲዳማ ክልል በሀዋሳ ከተማ ካሉ <u>ስምንት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ</u> ትምህርት ቤቶች አንዱ አዳሬ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 9ኛ ክፍል የሚማሩ በሲዳምኛ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ሰዋስዋዊ ስህተቶችን መፈተሽና መተንተን ሲሆን በአይነታዊ የምርምር ዘዴ ከተጠና በኋላ የገላጭ ትንተና ስልትን በመጠቀም ጥናቱ ይካሄዳል፡፡

## 3.1.የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በሲዳማ ክልል በሀዋሳ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ <u>ሰባት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ አንዱ</u> የሆነው አዳሬ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ላይ በአመቺ የአመራረጥ ዘዴ በመጠቀም ጥናቱ ይካሄዳል፡፡ ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ያለው (2009፡135) እንደሚከተለው አብራርተውታል፣ “ተመራማሪው ጥናቱን በቅርበት ባገኛቸውና ጥናቱን ለማካሄድ አመቺ በሆኑለት ሰዎች ወይም ነገሮች ላይ ተመርኩዞ ምርምሩን ሲያካሄድ አመች ንሞና መጠቀም ይችላል ብለዋል፡፡”በመሆኑም በዚህ ጥናት <u>አመች የናሙና ስልት</u> ተግባራዊ ሆኗል፡፡

## 3.2.የተማሪዎች ናሙና አወሳሰድ

ጥናቱ ትኩረት የሚያደርገው በሲዳምኛ ቋንቋ  አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ላይ በመሆኑ በተመረጠው ትምህርት ቤት ውስጥ አፋቸውን በአማርኛ የፈቱ ተማሪዎችና አማርኛ ኢ-አፍ ፈት የሆኑ ተማሪዎች በመኖራቸው በሲዳምኛ ቋንቋ  አፍ-ፈቶቹን በመለየት በክፍል ስንት ተማሪ እንዳለ በመለየት ከአምስት የዘጠነኛ ክፍል ሲዳምኛ አፍ-ፈት ተማዎች በድምሩ 120 ተማሪዎች በወሳኝ የንሞና ዘዴ በመምረጥ ጥናቱ ይካሄዳል፡፡ ይህ ዘዴ የተመረጠበትን ምክንያት ያለው (2009፡135) እንደሚከተለው ገልጸውታል፡-

በወሳኝ ናሙና ዘዴ ወቅት ከጥናቱ አካላይ መመረጥ የሚኖርባቸውን የናሙና አባላትን የሚወስኑት ተመራማሪው ራሱ፣የምርምሩና የጥናቱ አካላይ ባህሪ ይሆናል፡፡ይህም ማለት እነማን ወይም የትኞቹ የጥናቱ አካላይ አባላት በጥናቱ ውስጥ ናሙና ሆነው መመረጥ እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው የሚወስነው ዕጣ፣ ዕድል ወይም አጋጣሚ ሳይሆን በምርምሩ ባህሪ የተነሳ ተመራማሪው መረጃውን፣ከተወሰኑ ሰዎች ወይም ነገሮች እንዲሰበስብ ሲገደድ፣ተመራማሪው እነዚህን ብመረጣቸው ለምርምሩ አስፈላጊና በቂ መረጃ ይኖራቸዋል ብሎ ሲወስን ወይም ለምርጫ ዕድል ሳይኖረው መረጃ ሊያገኝ የሚችልባቸው ሰዎች ወይም ነገሮች በብዛት በጣም ውሱን ይሆኑና ናሙና መምረጥ አስፈላጊ ሳይሆን ሲቀር ካጠገቡ ባገኛቸው ሰዎች ወይም ነገሮች መረጃውን እንዲሰበስብ ሲገደድ የሚጠቀመው የናሙና ዘዴ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር የተመረጠው ትምህርት ቤት በአዋሳ ከተማ የሚገኝ ሲሆን በትምህርት ቤቱ ደግሞ የሚማሩት በአማርኛ አፋቸውን የፈቱና ከሲዳምኛ ተናጋሪዎች ውጪ የሆኑ ተማሪዎች አብረው ስለሚማሩ በሲዳምኛ አፍ-ፈቶች ላይ ብቻ ለመስራትና ጥናቱን አስተማማኝ ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡

## 3.3.የመምህራን ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት ተተኳሪ ያደረገው በሀዋሳ ከተማ በሚገኘው በአዳሬ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አፋቸውን በሲዳምኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ታላሚዎቹ ተማሪዎችን የሚያስተምሩ መምህራንን በጠቅላይ ናሙና አመራረጥ ዘዴ በመምረጥ ጥናቱ ይካሄዳል፡፡ ዘዴው የተመረጠበትን ምክንያት ያለው (2009፡135)እንደሚከተለው አብራርተዋል፡-"ተመራማሪው ያገኛቸውን ሁሉንም የጥናቱን አካላይ አባላት በጥናቱ ውስጥ ተሳታፊ አድርጎ ሲወስድ ጠቅላይ ንሞና ይባላል " በመሆኑም በአዳሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በቁጥር ጥቂት በመሆናቸው ለጥናቱ መረጃ አስተማማኝነት ሁሉንም በመረጃ ሰጪነት ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

## 3.4.የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን ዋና እና ዝርዝር አላማዎች ለማሳካት በተግባር ላይ የሚውሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች፡-

1. በተማሪዎች የሚጻፍ ድርሰት
2. ለታላሚ ተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ
3. ለመምህራን ቃለመጠይቅ

### 3.4.1.ተማሪዎች የሚጻፍ ድርሰት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የሆኑትን ታላሚዎቹን ተማሪዎች መምህራን በአማርኛ ድርሰት በሚያጽፋቸው ጊዜ የሚከሰቱ ችግሮችን በመለየት እንዲፈቱ፣በመማር ማስተማሩ ሂደት የአማርኛ ቋንቋን የጽህፈት ሥርዓት ለይቶ በማወቅ ለተግባቦት ለመጠቀም እና መምህራን ተማሪዎቹን ድርሰት አጽፈው ሲያርሙ የተከሰተውን ሰዋስዋዊ ስህተት ምንጭ በማወቅና በመለየት ምግቤ ምልሽ ለመስጠት በናሙናነት የተመረጡ በአዳሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት 120 ተማሪዎች ድርሰት እንዲጽፉ ተደርጓል፡፡

#### 3.4.1.1.የድርሰቱ ርዕስ አመራረጥ

ለጥናቱ መረጃዎቸን ሰብስቦ ለመተንተን የተመረጡትን 120 ታላሚ ተማሪዎችን ርዕስ መርጦ ማጻፍ ተገቢ ነው፡፡ይህንን ለማድረግ አጥኚዋና የትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጋራ በመሆን የተማሪዎቹን የክፍል ደረጃ፣ባህልና የአኗኗር ዘይቤ መሠረት ባለማድረግ ስድስት ርዕሶች አዘጋጅተዋል፡፡ ከነኚህ ርዕሶች ተማሪዎቹ በራሳቸው ፍላጎትና አስተሳሰብ እናውቀዋለን ወይም ሰፊ ሀሳብ እናገኛለን ብለው ያሰቡትን የፈለጉትን ሁለት ርዕስ መርጠው ሁለት ጊዜ በተለያየ ወቅት ጽፈዋል፡፡ ሁለት ጊዜ የጻፉበት ምክንያት የመጀመሪያው ሀሳባቸውን እንዴት አፍልቀውና አቀነባብረው እንደሚጽፉ ራሳቸውን የሚፈትሹበትና ለአጥኚዋ የስህተቶችን ዓይነት በማወቅ ምድብና መለያ በመሰየም የመጀመሪያ ዙር መረጃ በመሆን አገለግሏል፤ሁለተኛው ከመጀመሪያው በሀሳብ አደረጃጀትም ሆነ ፍሰት የተወሰነ መሻሻል ይኖራል ተብሎ ስለሚታሰብ እና ለጥናቱ ሰፊ ትንታኔ ለመስጠት ይረዳል በሚል እሳቤ ተከናውኗል፤ ደግሞም ሆኗል፡፡

#### 3.4.1.2.ድርሰቱ የታረመበት ስልት

ድርሰቶቹ ከተጻፉ በኋላ አጥኚዋን ጨምሮ አምስት የትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን ለስህተት አይነቶች በተሰየመው ምድብ በመከፋፈል ለእርማት አዘጋጅታለች፡፡ በመሆኑም ለመምህራኑ እርማት ከማድረጋቸው በፊት አጥኚዋ አምስት ወረቀቶችን አርማ ለስህተቶቹ ዓይነት መለያ(ኮድ) በመስጠት ኮፒ በመድረግ በአስተራረሙ ላይ የአንድ ቀን ስልጠና በመስጠት በሚከተሉት ስህተቶች ላይ አጽንኦት ሰጥተው እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡ የስህተት ዓይነቶቹ <u>የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት</u>፣ <u>የቋንቋ አወቃቀር ስህተት</u> እና <u>ምድብ የሌላቸው ስህተቶች ናቸው፡፡</u>

### 3.4.2. የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ

በዚህ ጥናት ከመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ አንዱ የሆነው የጽሁፍ መጠይቅ ለተጠኚ ተማሪዎቹ በማቅረብ በድርሰቱ ውስጥ ለተገኙት ሰዋስዋዊ ስህተቶች መንስዔ የሆኑ ነገሮችን ለማወቅ 120 ተማሪዎች መጠይቁን ሞልተዋል፡፡

### 3.4.3. የመምህራን ቃለመጠይቅ (ቃለ-መጠይቅ)

ጥናቱ በሚካሄድበት ትምህርት ቤት የሚገኙ ከአጥኚዋ ሌላ አራት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጥናቱ ተሳታፊ በመሆን የቃለመጠይቅ መረጃ ሰጥተዋል፡፡ መምህራኑ የሚሰጡት መረጃ ተማሪዎች ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ ለተሳሳቱት ሰዋስዋዊ ስህተት መንስዔ የሆኑትን ነገሮች በመጠቆም ተጨማሪ መረጃ ሆኗል፡፡

## 3.5. የመረጃ አጠነቃቀርና አተናተን

### 3.5.1. በተጠኚ ተማሪዎች የተጻፉ ድርሰቶች ትንተና

ጥናቱ በሀዋሳ አዳሬ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አፋቸውን በሲዳምኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶችን መፈተሽ ሲሆን በጥናቱ ዓላማ ላይ ለተጠቀሱት ዐብይና ዝርዝር ዓላማዎች ምላሽ በሚሰጥ መልኩ ይተነተናል፡፡ ተማሪዎቹ የጻፏቸው ድርሰቶች በአምስት መምህራን ከታረሙ በኋላ የስህተት ዓይነቶቹ የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት፣ የቋንቋ አወቃቀር ስህተት፣የሆሄያት ድግግሞሽ እና ምድብ የሌላቸው ስህተቶች በሚል ቀደም ሲል በተጠቀሱት የስህተት ዓይነቶች ሥር ተመድበዋል፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ ተማሪዎች በጻፉት ድርሰት ውስጥ የሚፈጽሙትን ስህተቶች ለመፈተሽ እና ለመተንተን ሥራ ላይ የሚውለው የNorish (1992) የስህተት ትንተን ስልት ይሆናል፡፡ የNorish (1983) የስህተት ትንተና አከፋፈል ሁለት ዘዴዎችን የያዘ ሲሆን የመጀመሪያው ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገና ሁለተኛው ስህተትን መሰረት ያደረጉ ዘዴዎች ናቸው፡፡ በዚህ ጥንት ተግባራዊ የሆነው ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረገውን የመጀመሪያው የስህተት ትንተናን ስልት ሆኗል፡፡

በዚህም መሠረት የመተንተኛው ቀመር በሚከተለው መንገድ ተዘጋጅቷል፡-

- በአንድ ድርሰት ውስጥ የሚገኘውን አማካይ የቃላት ብዛት ለማወቅ ድርሰቶቹ የተጻፉበትን የቃላት መጠን ለድርሰቶቹ ቁጥር በማካፈል ተወስኗል፣
- በአንድ ድርሰት ውስጥ በአማካይ ምን ያህል ስህተቶች እንዳሉ ለማወቅ የስህተቶቹን መጠን ለድርሰቶቹ ተካፍሏል፣

- አንድ ሰህተት በምን ያህል ቃላት ውስጥ እንደሚገኝ ለማወቅ አጠቃላይ የቃላቱን ብዛት ለአጠቃላይ የስህተት ብዛት ማካፈል፣በመቶ ቃላት ምን ያህል የስህተት ድግግሞሽ እንዳለ ለማወቅ የስህተቶችን መጠን በመቶ በማባዛት እና የተገኘውን ውጤት ድርሰቶቹ በተጻፉበት የቃላት ብዛት ማካፈል ተሰልቷል።

### 3.5.2. የመጠይቆች ትንተና

በዚህ ጥናት በታላሚ ተማሪዎቹ በተጻፈው ድርሰት ውስጥ የተከሰቱትን ስህተቶች የጽሁፉን ብቻ አይቶ የስህተቱን መንስዔ ለይቶ ማወቅ አልተቻለም።በመሆኑም የስህተቶቹን መንስዔ ለማወቅ ተጨማሪ መረጃ በማስፈለጉ የጽሁፍ መጠይቁ እና ቃለ መጠይቁ የወጥት ችግር ቃለ መጠይቅ በድርሰቱ ውስት ለተከሰተው ስህተት ደጋፊ የመረጃ ምንጭ በመሆን ቀርበው የተገኙት ምላሾች ወይም መረጃዎች  በገላጭ የትንተና ስልት ተንትነው ቀርበዋል።

# ምራፍ አራት

## 4. የጥናቱ ውጤት ትንተና

በዚህ ምዕራፍ ሥር ከተማሪዎች በድረሰት ጽሁፍ እና በጽሀፍ መጠይቅ የተየተሰበሰቡ መረጃዎች እንዲሁም ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡

### 4.1.በድርሰቶቹ ውስጥ የተስተዋሉ አጠቃላይ የስህተቶች ዓይነት እና ብዛት

በድርሰቶቹ ውስጥ የተስተዋሉ አጠቃላይ የስህተቶች ዓይነት እና ብዛት የተቆጠሩት በሁለት ዙር በተጻፉት ድርሰቶች ውስጥ ነው፡፡ በነኚህ ድርሰቶች ውስጥ የተጻፉት ቃላት ብዛት 22272 ሲሆኑ በነኚህ ቃላት ውስጥ የተገኙት የስህተት ብዛቶች በቁጥር 7996 በመቶኛ 36 ናቸው፡፡ ታላሚ ተማሪዎች ሁለቱን ድርሰት ለመጻፍ የተጠቀሙባቸው ቃላት ብዛት በአማካይ 92.8 ሲሆን በአንድ ድርሰት በአማካይ የተገኘው ስህተት 33.32 እና የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 36 ነው፡፡

ድርሰቶቹ በሁለት ዙር የተጻፉበት ምክንያት አንድ ጊዜ ብቻ ቢሆን ምናልባት የተሟላ መረጃ ላይሆን ይችላል ከሚል ጥርጣሬ የተነሳ የተሻለ መረጃ ለማግኘት ምንም ቢሆነ ከአንድ ሁለት ይሻላል በሚል  ነው፡፡ ድርሰቶቹን በሁለት ዙር ይጻፉ እንጂ ሁለቱንም ድረሰቶች የማነጻጸር ጉዳይ ስለሌለ አጠቃላይ ስህተቶችን በሚመለከት የቀረቡት መረጃዎች አጠቃላይ ድረሰቶቹንና ስህተቶቹ ላይ በመመርኮዝ ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን አጠቃላይ የስህተት ዓይነቶችንና ብዛታቸውን በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ባጭሩ ጠቅለል አርገን እናያለን፡፡

**ሠንጠረዥ1 አጠቃላይ የስህተት ዓይነት እና ብዛት**

| የድርሰቱ ዓይነት | የወረቀቱ ብዛት | ድርሰቱ የተጻፈበት ቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ በመቶ ቃላት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በቁጥር | በመቶኛ | | |
| ድርሰት አንድ | 120 | 10440 | 87 | 4012 | 38.43 | 33.43 | 38.43 |
| ድርሰትሁለት | 120 | 11832 | 98.6 | 3984 | 33.67 | 33.2 | 33.67 |
| ድርሰት አንድና ሁለት | 240 | 22272 | 92.8 | 7996 | 36 | 33.32 | 36 |

## 4.2. ዋና የስህተት ዓይነቶች ምድቦች

ቀደም ሲል በምዕራፍ ሶስት እንደተገለጸው በድርሰቶቹ ውስጥ የታዩ አብይ የስህተት ዓይነቶቹ የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት፣ የቋንቋ አወቃቀር ስህተቶቸ እና ምድብ የሌላቸው ስህተቶች እንደሚከተለው በዋናነት ተመድበዋል።

በሁለቱም ዙር ከተጻፉት ድርሰቶች አብላጫውን የስህተት ዓይነት የያዘው የቋንቋ አጠቃቀም ምድብ ነው፤በአጠቃላይ ከተቆጠሩት እና ከተለዩት 7996 ስህተቶች ውስጥ 3997ቱ 36.05 በዚህ ምድብ የተለዩ ናቸው። በአንድ ድርሰት ውስጥ የተከሰቱት አማካ ስህተተቶች 33.7ሲሆኑ አማካይ የስህተት ድግግሞሹ 36.43 ናቸው።

ከቋንቋ አጠቃቀም በመቀጠል ከፍተኛ የስህተት መጠን የተለየው የቋንቋ አወቃቀር ስህተት ነው። የኸውም ከአጠቃላይ ስህተቶች 7996 ውስጥ 3800 34.25 የተሸፈነው በዚሁ የምድብ ስህተቶች ነው። በአንድ ድርሰት ውስጥ የተገኙት አማካይ ስህተቶች 35.11 ሲሆኑ አማካይ የስህተት ድግግሞሹ 38.16 ሆኗል።

በመጨረሻም የተቆጠሩት በዓይነት ለመመደብ ወይም ለመለየት ያልተቻሉ የስህተት ክፍሎች ሲሆኑ ከአጠቃላይ ስህተት 199 ስህተቶች ተለይተዋል፤ በዚህ ምድብ በአንድ ድርሰት ውስጥ የተከሰቱት አማካይ ስህተቶች 1.68 ሲሆኑ የስህተት ድግግሞሹ 1.82 ነው። እነኚህን ከላይ የተገለጹትን ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶችን በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ጠቅለል አርገን እናያለን።

***ሠንጠረዥ ሁለት ዋናዋና የስህተት ዓይነቶች እና ምድቦች***

| የስህተት ዓይነት ምድቦች | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት ብዛት በቁጥር | የስህተት ብዛት በመቶኛ | አማካይ ስህተት | የስህት ድግግሞ | የስህተ ብዛት በቁጥር | የስህተት ብዛት በመቶኛ | አማካ ስህተ | የስህተት ድግግሞ | የስህተ ብዛት በቁጥር | የስህተት ብዛት በመቶኛ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ |
| የቋንቋ አጠቃቀ | 2003 | 19.2 | 16,69 | 19.2 | 1994 | 16.85 | 17.01 | 17.25 | 3997 | 36.05 | 33.7 | 36.43 |
| የቋንቋ አወቃቀ
 | 1901 | 18.21 | 18.84 | 21.66 | 1899 | 16.04 | 16.27 | 16.5 | 3800 | 34.25 | 35.11 | 38.16 |
| መመደ ያልተ | 108 | 1.03 | 0.9 | 1.03 | 91 | .77 | 0.78 | .79 | 199 | 1.8 | 1.68 | 1.82 |
| ድምር | 4012 | 38.43 | 33.43 | 38.43 | 3984 | 33.67 | 34.15 | 34.63 | 7996 | 72.1 | 67.58 | 73.06 |

በሠንጠረዡ ውስጥ የቋንቋ አጠቃቀም አወቃቀር፣መመደብ ያልተቻሉ እነኚህ ገጽ 3 ላይ ቀልመዋል ለምን ትጠይቅ

### 4.2.1.የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት

በሠንጠረዥ ሁለት በቋንቋ አጠቃቀም ስር እንደታየው ከሶስቱ የስህተት ምድቦች ውስጥ ይህ ምድብ ከፍተኛውን ቁጥር እንደያዘ አይተናል፤በዚህ የምድብ ስህተት ውስጥ የሚከተሉት ንዑሳን የስህተት ዓይነቶች ይገኛሉ፡፡እነርሱም የሆሄያት ቅርጽ ስህተት፣የሆሄያት ግድፈት ስህተት እና የቃላት ድግግሞሽ ስህተቶች ናቸው፡፡ እነዚህን እንደሚከተለው በዝርዝር እናያቸዋለን፡-

#### 4.2.1.1. የሆሄያት ቅርጽ ስህተት

ተማሪዎቹ በሁለት ዙር በጻፉት ድርሰት ውስጥ 3997 ከቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች 1249 የተቆጠሩት የሆሄያት ቅርጽ ስህተቶች ናቸው፡፡ ከነዚህ ስህተቶች 12.72 አማካይ ስህተት ሲሆን 6.85 የስህተት ድግግሞሽ ነው፡፡ አንድን መልዕክት በጽሁፍ ለማስተላለፍ ወይም ለመግለጽ ሲታሰብ የቋንቋውን ድምጽ የሚወክሉትን ሆሄያትን በትክክል ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ይህን በተመለከተ Byrne (1988:1) "የአንድ ቋንቋ ተጠቃሚዎች ትርጉም ሊሰጡ የሚችሉ የንግግር ድምጾችን የሚወክሉ ሆሄያትን በሥርዓት በማቀናጀት ቃላትን በመመስረት ሀሳብን ወይም መልዕክትን ማስተላለፍ እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡"

በሆሄያት ቅርጽ ስህተት ውስጥ የተገኙት ስህተቶች በአማርኛ የፊደል ገበታ ውስጥ ማይገኙ ቅርጽ ያላቸውን ሆሄያት በድርሰቶቹ ውስጥ መታየታቸው  እና ሆሄያትን ባልተገባ ቦታ መጠቀማቸው ተደርሶበታል፡፡ በመሆኑም የሆሄያት ቅርጽ ስህተቶችን በሶስት ከፍለን እናያቸዋለን፡፡ የመጀመሪያው የሆሄያትን ቅርጽ እንዳለ በመቀየር የታየ ስህተት፣ሁለተኛው አንዱን ሆሄ በሌላ በመተካት የተከሰተ ስህተት፣ሶስተኛው ስህተት ውህድ ሆሄያትን ባለመጠቀም የተከሰቱ ስህተቶች ናቸው፡፡ እነኚህን ስህተቶች ከድርሰቶቹ ውስጥ ለአብነት እየጠቀስን እናያለን፡፡

- **የሆሄያት ቅርጽን መቀየር**

ይህ የሆሄ ቅርጽ የስህተት ዓይነት በአብዛኛው ድርሰቶች ውሰጥ የታዩ ችግሮች ናቸው፡፡በመሆኑም ለምሳሌ ያህል ከሌሎች ስህተቶች ጋር የ‹‹ሲዳማ ባህላዊ ዳኝነት››በሚለው ድርሰት ከጻፉት የተወሰደ ለአብነት እንደሚከተለው ተጠቅሷል፡፡ በ (   ) ቅንፍ የተጠቆመው የቅርጽ ለውጥ የተደረገባቸውን ሆሄያት ለማመልከት ነው፡፡

- ቤ(ቅ)ድማ(ያ) ሁለ(ት) ሰ(ዎ)ች (ይ)ጥለል
- (አ)ንደኛው (ያ)ሳው(ቃ)ል (አ)ሰውቃ በሁላ (ሻ)ማገሌዎ(ች) ይ)(ሰ)በሰባሉ
- በ(ማ)ለ()ት (ያ)ደርሳል ስመ(ዎ)(ም) (ኤ)ንፈሙት( አ)ድርስ በ(ማ)ለት…

ከላይ በተጠቀሱት ምሳሌዎች ውስጥ ምናየው የሆሄያት የቅርጽ ስህተት በነዚህ በሶስት ምሳሌዎች እንኳ ምን ያህል ተመሳሳይ ሆሄያት ተደጋግመው እንደተገኙ እንመለከታለን፡፡ ስህተቶቹ በአብዛኛዎቹ ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የተገኙ ናቸው፡፡በተለይ የ(ይ) እና (አ) ዝርያዎች ጎልተው የሚታዩ ስህተቶች ናቸው፡፡ የነዚህ ስህተቶች መከሰቻ ምክንያት ገና ቋንቋውን መማር ሲጀምሩ ከሥር መስተካከል እና ትክክለኛውን ቅርጽ ሳያሳዩ በመቅረት የተፈጠሩ ይመስላል ፤ ምክንያቱም ተማሪዎቹ በነበሩት ሆሄያት (ፊደላት) ላይ ተጨማሪ የአጻጻፍ ቅርጽ በመፍጠር መደበኛውን ሆሄ አጥፍተውታል፡፡ በተጨማሪ ( አባሪ 1 ይመልከቱ)

- **ሆሄያትን በሌላ ሆሄያት መተካት**

ይህ ስህተት የሚከሰተው የቋንቋውን ሆሄያት ለይቶ ካለማወቅ የተነሳ የሚፈጠር ድምጽ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ለአብነት የ‹‹ሲዳማ ባህላው ምግብ›› ከሚለው የተወሰደውን ለአብነት እንይ፡-

- (ቤ)መጀመ(ረ)ያ ሼጥ ቤት የማስ(ሬ)ው…
- ቤመቀጠል (ጋ)ሜት(ሬ) ጉድ(ን)ድ ያቆ(ፉ)ራል…
- ዬቤቱ አባወ(ረ)የአካባቢውን (ሰ)ማ(ጋ)ሌዎ(ት)…

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የተጠቀሱት ስህተቶች በቅንፍ ( ) ተጠቁመዋል፡፡ የተሰጡትን ምሳሌዎች እያንዳዳቸውን ስናይ በመጀመሪያው ላይ በቅንፍ የተጠቆመው ሳልሱ (ቤ) ግዕዙን /በ / ተክቶ የገባ ነው፤በተመሳሳይ ሳልሱ (ሬ) የግዕዙን /ረ/ን ተክቶ የገባ ነው፡፡ ግዕዙ በሳልሱ የመተካካቱ ምክንያት በተጠኚ ተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ላይ ግዕዙ /ኧ/ ያለመኖርን ያመለክተናል፡፡ በሚቀጥለው ምሳሌ ላይ በዓረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ላይ የምናየው ስህተት ከላይኛው ጋር ተመሳሳይ ሲሆን በዚሁ ዓረፍተ ነገር (ጋመ)ት(ሬ) እና ጉድ(ን)ድ ያቆ(ፉ)ራል የሚሉት ቀጥታ በሆሄ ቦታ የተተኩ ሆሄያቶች ናቸው፡፡ተክተው የገቡት ወይም ቀይረው የገቡት ከዓረፍተ ነገሩ ዐውድ አንፃር (ጋመ )እና (ሬ) (ፉ) =/በሜ/ን እና/ር/ን ይሆንና ሲስተካከል **ጋሜትሬ** = በሜትር ይሆናል **ጉድንድ** /ን/ተክታ የገባቸው/ጓ/ን ነው፤የስህተቱ መንስዔ የአማርኛውን ሆሄ ለቦታው ቅንጅት የሚያስፈልገውን ሆሄ አጣርቶ ካለማወቅ ይመስላል፡፡ (በተጨማሪ አባሪ 2 ይመልከቱ)

- **የውህድ (ውስብስብ) ድምጾች ሆሄያት ያለመጠቀም ስህተት**

የእነኚህ ስህተቶች መከሰቻው ምክንያት የሚሆነው በተጠኚ ተማሪዎች አፍ-መፍቻ ቋንቋ ውስጥ ያለመገኘት ይሆናል፡፡ የ‹‹ሲዳማ ባህላዊ ምግብ ›› በሚለው ድርሰት ከተጻፈው እስቲ ለአብነት እንይ፡-

- ቡርሳሜ ኬቴሰራ በ(ሀ)ላ ቤወተቲ ዩቤላል
- ቆጮ ኬቴዘጋጄ ቤጉዲ(ጋ)ድ ይዜፌዘፋል
- ቡርሳሜ ኬተሰራ ቤ(ሀ)ላ ኢናት ለራ(ሳ)ቡዙም አቲበላም

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ በዓረፍተ ነገሮቹ ውስጥ በቅንፍ የተጠቆሙት የሆሄያት ስህተት ቤ(ሀ)ላ፣ቤጉዲ(ጋ)ድ እና ለራ(ሳ) የሚሉት ተክተው የገቡት ውህድ ድምጾችን /ኋ/፣/ጓ/እና / ሷ/ ናቸው። የእነኚህ ውህድ (ውስብስብ ) ድምጾችን (ሆሄያትን) ያለመጠቀም ችግር በተጠኚ ተማሪዎች የአፍመፍቻ ቋንቋቸው ውስጥ ያለመኖር የፈጠረው ስህተት ነው። ስለዚህ በአማርኛው ቋንቋ ሲስተካከል ቡርሳሜ ከተሰራ በኋላ በወተት ይበላል

ቆጮ ከተዘጋጀ በጉድጓድ ይዘፈዘፋል

ቡርሳሜ ከተሰራ በኋላ እናት ለራሷ ብዙም አትበላም ይሆናል

ከዚህ በላይ ያየነው በሆሄያት ቅርጽ ስህተት ማለትም ሆሄያትን በሌላ ሆሄ መተካት እና የውህድ (ውስብስብ) ድምጾች (ሆሄያት) ያለመጠቀም ስህተቶችን ስናይ መንስዔያቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ውስጥ በሌሉ አናባቢ እና ተናባቢ ሆሄያት (ድምጾች) ምክንያት የተፈጠሩ ስህተቶች ናቸው። በአማርኛ እና በሲዳሚኛ ቋንቋ ውስጥ ያለው የኣናባቢዎች ልዩነት እንደሚከተለው እናያለን። የአማርኛ አናባቢዎችን ጌታሁን (2011፡16) "በአማርኛ ውስጥ የምናገኛቸው አናባቢ ድምጾች ሰባት ሲሆኑ፤እነሱም /እ፣ኡ፣ኢ፣ኣ፣ኤ፣እ፣ኦ/ ናቸው በማለት ገልጸዋል። "የሲዳሚኛ አና ባቢዎች /ኡ፣ኢ፣ኣ፣ኤ፣ኦ/ ናቸው።በእነኚህ አናባቢ ልዩነቶች በሲዳሚኛው ላይ ባልተገኙት የአማርኛው /ኧ እና እ/ የቁጥር ብቻ ሳይሆን የቅርጽ እና የይዘትም ልዩነት አላቸው።ይህ ልዩነት ደግሞ በሁለቱም ቋንቋዎች መሀከል የቃላት አቀነጻጀት ልዩነት ፈጥሯል።

የተናባቢ ሆሄያት (ድምጾች) ልዩነት በሲዳሚኛ ላይ የማይገኙ በአማርኛ ቋንቋ ላይ የሚገኙ ተናባቢዎች / ቭ፣ሸ፣ች፣ጭ፣ፕ፣ጵ፣ፅ እና ውስብስብ ድምጾች /ናቸው ከውስብስብ ድምጾች ለአብነት /ጓ፣ኳ፣ቋ/ የእነኚህ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ላይ አለመኖር ተማሪዎቹ በጻፉት ድርሰት ላይ ለስህተት እንደ መንስዔ ሆነው ታይተዋል።(አባሪ 3 እና 4 ተመልከቱ)

በተጻፉት ድርሰቶች ውስጥ የተከሰቱት ስህተቶች የአፍ መፍቻ (የሲዳምኛ) ቋንቋ ተተጽእኖ በግልጽ ታይቷል፤በተጨማሪ በተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅና በመምህራን ቃለመጠይቅ እንዴት እንደተባለ ቀጠለን እናያለን።

ሰንጠረዥ 3፡ በአማርኛ ስትጽፍ /ፊ/ በይበልጥ የሚያስቸግርህ /ሽ/ ክፍል የትኛው ነው

| በአማርኛ ስትጽፍ /ፊ/ በይበልጥ የሚያስቸግርህ /ሽ/ ክፍል የትኛው ነው | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| ሀ/በቃላት ድምጾችን በተገቢው ፊደል | 12 | 10 |
| ወክሎ አለ መጻፍ | 26 | 21.67 |
| ለ/መደብ አመልካች ቅጥያዎችበትክክል | | |
| አለመጻፍ | 6 | 5 |
| ሐ/ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ | 13 | 10.83 |
| ተጠቅሞ አለመጻፍ | 63 | 52.5 |
| መ/ሀሳብን ትክክል አቀናብሮ መፃፍ | | |
| ሠ/ከላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች ሁሉ | | |
| ድምር | 120 | 100.0 |

የዚህ መጠይቅ ዓላማ ተማሪዎቹ በአማርኛ ስጽፉ በይበልጥ የሚያስቸግራቸው የትኛው የጽህፈት ክንውን እንደሆነ ለመገንዘብ የቀረበ ጥያቄ ነው፡፡በዚህ መሠረት የ120 ተጠኚ ተማሪዎች ምላሽ እንደሚከተለው እናያለን፡-ከ120 ተጠኚዎች በቃላትድምጾችን በተገቢው ፊደል ወክሎ መጻፍ 12(10%)መደብአመልካችቅጥያዎችበትክክል አለመጻፍ 26(21.67% ) ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ ተጠቅሞ አለመጻፍ 6(5% )ሀሳብን በትክክል አቀናብሮ መፃፍ 13(10.83% ) ከላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች ሁሉ ያስቸግረኛል 63 (52.5%)የሚለውን አማራጮች መርጠዋል ፤ይሁን እንጂ ከተጠኚዎች ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑቱ ወይም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የሁሉም ችግር ወይም በቃላት ድምጾችን በተገቢው ፊደል ወክሎ አለመጻፍ ፣ መደብ አመልካች ቅጥያዎችን በትክክል አለመጻፍ፣ ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ ተጠቅሞ አለመጻፍ እና ሀሳብን በትክክል አቀናብሮ አለመጻፍ ችግር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡የዚህ ችግር መንስኤ በድርሰቱ ውስጥ እንደታየው ከሆነ የሲዳምኛውንና የአማርኛውን ሆሄያት ልዩነት ለይቶ ካለማወቅ የተነሳ፣በአማርኛ ሆሄያት ውስጥ የሚገኙትን የአናባቢዎችንና የተናባቢዎችን አቀነጻጀት አፍ ከፈቱበት ቋንቋ አንጻር ለመጻፍ የሚያደርጉት ጥረት እና የሲዳምኛውን ቋንቋ መዋቅር በአማርኛው የመጠቀም ሂደት ሲሆን በአጠቃላይ የአፍ-መፍቻ ቋንቋቸው ተጽእኖ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

ሠንጠረዥ 4፡የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖን በተመለከተ የቀረቡ የመመዘኛ መጠይቆች

| | በጣምከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣምዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 3. ያለህበት/ሽበት ያንቺ/ያንተ ቋንቋ ከአማርኛ ቋንቋ ጋር ያለው ልዩነት ምን ያህል ነው? | 40.0% | 50.0% | 10.0% | 0.0% | 0.0% |
| 4.የአፍ-መፍቻቋንቋህ/ሽ/ አማርኛቋንቋን በጽህፈት ጊዜ እንደልብህ/ሽ/ እንዳትጠቀም ያሳደረብ/ሽ / ተጽዕኖ | 35.0% | 40.0% | 25.0% | 0.0% | 0.0% |

የዚህ መጠይቅ ዓላማ ድርሰት ሲጽፉ ለተከሰተው ሰዋስዋዊ ስህተት መንስዔ ያደጉበት አካባቢ ከአማርኛ ቋንቋ ጋር ያለው ልዩነት እና የአፍ-መፍቻ ቋንቋቸው ተጽእኖ አማርኛ ቋንቋን በጽህፈት እንደልብ እንዳይጠቀሙ ችግር ይፈጥር እንደሆን ለመገንዘብ ነው፡፡በመሆኑም ያደክበት /ሽ/አካባቢ አማርኛ ተናጋሪዎች ጋርያለው ልዩነት ለሚለው ጥያቄ 40.0%በጣም ከፍተኛ፣50.0% ከፍተኛ፣10.0% መካከለኛ እናቀሪዎቹ መመዘኛዎች ባዶ በመሆን ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ይህልዩነት በቀጥታ ተጽእኖ ባይፈጥርም በተዘዋዋሪ ለችግሩ ድጋፍ መሆኑ አይቀርም ምክንያቱም ይህ ልዩነት በሚጻፈው ድርሰት ላይም ልዩነት መፍጠሩ ስለማይቀር፡፡

የ4ኛው መጠይቅ አላማ አማርኛ ቋንቋን እንደፈለጉ ለመጠቀም የአፍ-መፍቻቋንቋ ተጽእኖ ፈጥሮ እንደሆነ ለማወቅ ነበር፡፡የተማሪዎቹ ምላሽ በጣም ከፍተኛ35.0%፣ከፍተኛ 40% መካከለኛ25%፣ ዝቅተኛ እና በጣም ዝቅተኛ ባዶ በመሆን ተመልሷል፡፡ከተማሪዎቹ ምላሽ የምንረዳው የአፍመፍቻ ቋንቋቸው አማርኛን በጽህፈት እንደፈለጉ ለመጠቀም ችግር እንደሚፈጥርባቸው ነው የምንገነዘበው ምክንያቱም የአብዛኛዎቹ ተማሪዎች ምላሽ ስናይ አማርኛቋንቋን በጽህፈት ጊዜ እንደልብ ለመጠቀም የአፍ-መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ እንዳለው 75 % በጣም ከፍተኛ እና ከፍተኛ በማለት በጋራ የመለሱት ምላሽ ያመለክተናል፡፡

ጥያቄ1፡.እርስዎ የጽህፈት መልመጃዎችን ሲያርሙ በአብዛኛው ተማሪዎች የሚፈጽሟቸው የስህተት አይነቶች የትኞቹ ናቸው?

መምህር 1፡‹‹ፊደላትን በተለይ ሳልስና ሳድስን ለይቶ አለመጠቀም ነው የሚታየኝ፡፡››

መምህር2፡‹‹እንደሚናገሩትም ስለሚጽፉ በአብዛኛው የሲዳምኛ አጠቃቀም ራብእ እና ሀምስ ግእዙን ፊደል እየለወጡ ስለሚጠቀሙ የሚታየውም የግእዝ ፊደል አጻጻፍ ስህተት ነው፡፡››

መምህር 3፡‹‹የአማርኛን ቃላት አስተካክለው ያለመጻፍ ስህተት ይታያል፡፡››

መምህርት 4፡‹‹የአማርኛን ፊደሎች አስታካክለው አይጽፉም በተለይ የመጀመሪያ ረድፍ ፊደሎችን አይጽፉዋቸውም፡፡››

ምላሻቸውን ስናጠቃልል መምህራን መልመጃዎችን ሲያርሙ በአብዛኛው ተማሪዎች የሚፈጽሟቸው የስህተት አይነቶች ከሆሄ(ፊደል) እና ቃላትን ለይቶ እና አውቆ ያለመጻፍ ችግር ነው ይህ ደግሞ የአፍ መፍቻ ቋንቋን እና የአማርኛውን ቋንቋ ሆሄያት(ፊደላት እና ድምጾች አጠቃቀም ለይቶ ካለማወቅ እና ከመጠቀም አንጻር የተፈጠረ ችግር ነው፡፡

ጥያቄ2፡ እርስዎ ተማሪዎች በጽሁፍ ሀሳባቸውን ሲገልፁ ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች መንስኤ ናቸው ብለው የ ሚገምቷቸውን ምክንያት ዘርዝሯቸው

መምህር 1፡‹‹በሲዳሚኛ ቋንቋ የሌሉትን የአማርኛ ፊደላት መጻፍ ስለማይችሉ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተጽእኖ ሳያደርግ አይቀርም››

መምህር 2፡ ‹‹የሚጽፉት አማርኛውን እንደሚናገሩት ስለሆነ የሲዳምኛ ቋንቋ ተጽእኖ ሳያደርግባቸው አይቀርም፡፡››

መምህር 3፡ ‹‹አማርኛ ሲናገሩ ግእዙን ፊደል ስለማይጠሩ የሲዳምኛ ቋንቋ ችግር ሳይሆን አይቀርም››

መምህርት 4፡ሲዳሚኛ ኩሽቲክ ነው አማርኛ ሴሜቲክ ነው ስለዚህ የኩሽቲክ ተናጋሪዎች የሴም ፊደላቶችን አንዳንዶችን በትክል መጥራት አይችሉም፡፡››

ምላሻቸውን ስናጠቃልል፡-በሲዳሚኛ ቋንቋ የሌሉትን የአማርኛ ፊደላት መጻፍ ስለማይችሉ፣ የሚጽፉት አማርኛውን እንደሚናገሩት ስለሆነ የሲዳምኛ ቋንቋ ተጽእኖ፣አማርኛ ሲናገሩ ግእዙን ፊደል ስለማይጠሩ የሲዳምኛ ቋንቋ ችግር እና የኩሽቲክ ተናጋሪዎች የሴም ፊደላቶችን አንዳንዶችን በትክል መጥራት ወይም መጻፍ ስለማይችሉ የሚሉት የምላሻቸው ፍሬ ነገሮች ናቸው፤ዞርዞሮ እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ግብ የሚያደርጉት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖን ነው፡፡

ጥያቄ 4፡. ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የጽህፈት ትምህርትን አስመልክቶ እንዴት ማሻሻል(መለማመድ) እንዳለባቸው አስተያየት ቢገለፁልን ለሚለው መጠ

መምህር1፡‹‹በአማርኛ እና በሲዳምኛ ፊደላት (ሆሄያት)መካከል ያለውን ልዩነቶች በ9ኛ ክፍል ሳይሆን ከዝቅተኛ ክፍል ጀምሮ እየለዩ እና እየተለማመዱ መምጣት አለባቸው፡፡››

መምህር 2፡ ‹‹ከፊደል ጀምሮ ቃላትን አረፍተ ነገርን እና ከዚያ በላይ ያሉትን የአማርኛውን የጽህፈት ሥርአት ከ5ኘ ክፍል ጀምሮ በትኩረት ማለማመድ ይገባል፡፡››

መምህር 3፡‹‹ተማሪዎቹ በአብዛኛው የሚቸገሩት በሣድስ እና ሣልስ እንዲሁም በሁለቱም ቋንቋ ያሉትን አናባቢዎች ለይቶ የመጻፍ ጉዳይ በመሆኑ በእነዚህ ላይ ከዝቅተኛ ክፍል ጀምሮ ቢሰራባቸው የተሸለ ይሆናል፡፡›

መምህርት 4፡‹‹ማስተማሪያ መጽሀፍ ሲዘጋጅ ባጭሩ የሲዳማ ተማሪዎችን ዳራ ያላገናዘበ በፌዴራል ደረጃ ቢሆንም አማርኛ 2ኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎችን ያለገናዘበ ስለሆነ ለወደፊቱ የጋራ የሚያደርግ መጽሀፍ ቢዘጋጅ ለመማር ተነሳሽነት ይኖራል፡፡ሌላው የሲዳማ ተወላጆች በአብዛኛወ የሚታወቁበት አማርኛ ሲናገሩም ሆነ ሲጽፉ በአማርኛ ግእዝና ሳድስ ቦታ ራብእንና ሀምስን ሲጠቀሙ ነው ይህንን ለማስተካከል ትኩረት ሰጥቶ ቢሰራ መሻሻል ይኖራል ብዬ አስባለሁ፡፡ ››

የአራቱም መምህራን ምላሽ ሲጠቃለል አገላለጻቸው በጥቂቱ ይለያይ እንጂ ጭብጡ አንድ ነው፤ ይኸውም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽእኖ ወይም ችግር ነው፡፡እንደው ለአብነት እንኳ ከአራቱም ምላሾች ሀይለ-ቃላቸውን ቀነጫጭበን ብንወስድ፣

መምህር1፡‹‹በአማርኛ እና በሲዳምኛ ፊደላት (ሆሄያት)መካከል ያለውን ልዩነቶች በ9ኛ ክፍል ሳይሆን ከዝቅተኛ ክፍል ጀምሮ እየለዩ እና እየተለማመዱ በመጡ፣መምህር 2፡ ከፊደል ጀምሮ ቃላትን አረፍተ ነገርን እና ከዚያ በላይ ያሉትን የአማርኛውን የጽህፈት ሥርአት ከ5ኘ ክፍል ጀምሮ በትኩረት ቢለማመዱ፣መምህር 3፡ተማሪዎቹ በአብዛኛው የሚቸገሩት በሣድስ እና ሣልስ እንዲሁም በሁለቱም ቋንቋ ያሉትን አናባቢዎች ለይቶ የመጻፍ ጉዳይ በመሆኑ በእነዚህ ላይ ከዝቅተኛ ክፍል ጀምሮ ቢሰራባቸው መምህርት4፡የሲዳማ ተወላጆች በአብዛኛወ የሚታወቁበት አማርኛ ሲናገሩም ሆነ ሲጽፉ በአማርኛ ግእዝና ሳድስ ቦታ ራብእንና ሀምስን ሲጠቀሙ ነው ይህንን ለማስተካከል ትኩረት ሰጥቶ ቢሰራ አራቱም የተናገሩት በደርርሰቱ ውስጥ የታዩትን አብይ ስህተቶችን ነው፤ስለዚህ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ችግር መሆኑ ግልጽነው፡፡

#### 4.2.1.2.ግድፈት

የግድፈት መንስኤ ባጭሩ በውጫዊ ወይም በውስጣዊ በሆነ ነገር ባለማስተዋል በድንገት የሚፈጠር ሆኖ ጸሀፊው ወይም ተናጋሪው ወደ ማስተዋል ሲመለስ በራሱ የሚያርማቸው ወይም የሚያስተካክላቸው እንደሆነ ነው፡፡ከዚህ አንጻር በሁለቱም ዙር ተማሪዎቹ በጻፉት ድርሰቶች ውስጥ የተገደፉ ሆሄያት1249 (5.61) ናቸው፤አማካይ ስህተት 10.41 ሲሆን የስህተት ድግግሞሽ 5.61 ነው፡፡እነኚህ ስህተቶች በመኖራቸው የጽሁፉን መልዕክት ወይም ሀሳብ አዛብተዋል፡፡በድርሰቶቹ ውስጥ ከተለዩት ስህተቶች መካከል ተማሪዎቹ ስለሲዳማ‹‹እርቅ ስርዓት››ከጻፉት ለምሳሌ የሚከተሉትን እናያለን፡-

- ሌሺምጊሊና ቤቲልቅ ዛፍ ( )ዪቂመጣሉ…
- ጢፋተኛ ጢፋቱን ( ) ይቅርታ ይጠይቃል…
- ዬቴበዳዩን ኢጅ ቤባሂሉ ሜሰረት ( ) ያደርጉታል…

ለግድፈቱ ምክንያት ሲጽፉ በመቸኮል ወይም በሂሊናቸው ሌላ ነገር በማሰብ በመጻፋቸው ነው እንጂ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ጋር የተገናኘ አይደለም፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያው ዓረፍተነገር ላይ የተገደፈው(የተጎረደው) በቅንፍ ውስጥ የሌለው /ይ/፣በሁለተኛው ላይ የተገደፈው (የተጎረደው)/ይ/ እና በሶስተኛው ላይ የተገደፈው/ዲ/ናቸው፡፡ከቃሉ ውስጥ የእነኚህን መጎረድ ወይም የዓረፍተነገሩን አውድ ላልተረዳ ሰው(አንባቢ)ትርጉሙን ለማወቅ ወይም ከጽሁፉ ጋር ለመግባባት ይቸገራል፡፡በመሆኑም ሲስተካከሉ እንደሚከተለው ይሆናሉ፡-

- ለሽምግልና በትልቅ ዛፍ /**ስር** /ይቀመጣሉ…
- ጥፋተኛ ጥፋቱን/ **አምኖ**/ይቅርታ ይጠይቃል…
- የተበዳዩን እጅ በባህሉ መሰረት /**እንዲስም**/ ያደርጉታል…(አባሪ 1 እና 5 ይመልከቱ)

#### 4.2.1.3.ያልተለዩ ስህተቶች

የዚህ ስህተት መከሰቻው የምንጽፈውን ጽሁፍ ልክ እንደምንናገረው ስለምንጽፈው ነው፡፡በዚህ የስህተት ዓይነት ወይም ምድብ ውስጥ ከጠቅላላው 7996 ስህተት ውስጥ 712 (3.2) ያልተለዩ ስህተቶች ናቸው፡፡ አማካይ ስህተት 5.97 ሲሆን የስህተት ድግግሞሹ 3.2 ነው፡፡እነኚህን ስህተቶች ለአብነት በሲዳማ ‹‹ባህላዊ ምግብ አሰራር ላይ ከጻፉት ድርሰት የተወሰደውን እናያለን››

ቡርሳሜ ሌመስራት ሴቶች (ተሰብሰብቼ) እንሰራለን…

ሚግቡ ከተሠራ በሀላ (አንድጋ)ተሰብስበን እንበላለን…

ቡርሳሜ እየተሰራ ( ወቶ)የሄደ ሰው ዪቀጣል…

በቅንፍ ውስጥ የተገለጹት የአማርኛ ቋንቋ የጽህፈት ሥርዓትን ያፋለሱ የዓረፍተነገር አጠቃቀም ስርዓትን የጣሱ ታላሚ ተማሪዎቹ እንደሚናገሩት የጻፉት በመሆኑ አንብቦ ለመረዳት አዳጋች ይሆናል፡፡በመሆኑም በአማርኛው ቋንቋ አጠቃቀም ሥርዓት ስናስተካክለው፡-

ቡርሳሜ ለመስራት ሴቶች /**ተሰብስበን**/ እንሰራለን

ምግብ ከተሰራ በኋላ /**በአንድላይ**/ ተሰብስበን እንበላለን

ቡርሳሜ እየተሰራ /**ወጥቶ**/ የሄደ ሰው ይቀጣል (አባሪ 3 እና 4 ይመልከቱ)

### 4.2.1.4.የቃላት ድግግሞሽ

በቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ውስጥ ካሉት ንዑሳን ስህተቶች ውስጥ 510 (2.3) የተሸፈነው በቃላት ድግግሞሽ ስህተት ነው፡፡በአንድ የድርሰት ጽሁፍ ውስጥ በአማካይ 4.25 የሚገኙ ሲሆን የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 2.3 ሆኗል፡፡የቃላት ድግግሞሽ ስህተት በጽሁፍ ውስጥ ሲገኝ በጸሀፊው እና በአንባቢ መሀከል የሰመረ ግንኙነት አይኖርም፡፡የዚህን ክስተት ተማሪዎች ስለ ሲዳማ ‹‹ፍቼ ጨምበለላ በዓል አከባበር››ከጻፉት ድርሰት ለአብነት የሚከተለውን እናያለን፡-

/**ቤመጀመሪያ አንደኛ**/ ቄን ዬዋዜማ ቄን ፌጠራ ዪባላል…

ኬዚያም /**ለሁለተኛ ሁለተኛ**/ ቀን ቴጌናኘተው ዪጨፍራሉ…

ከላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች የሚገልጹልን በዓረፍተነገር ውስጥ የቃላት ድግግሞሽ መኖር በቀጥታ ሊተላለፍ የተፈለገውን የጽሁፍ መልዕክት በተወሰነ መልኩ ያደበዝዘዋል፡፡ በማጉላት እና በስላሽ ከተገለጹት አንዱን ብቻ ቢጠቀሙ አረፍተነገሩ ለአንባቢ ግልጽ ይሆናል፡፡በአማርኛው ቋንቋ የአጻጻፍ ስርአት ሲስተካከሉ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

/**በመጀመሪያ**/ ቀን የዋዜማ ቀን ፊጠራ ይባላል

ከዚያም /**ሁለተኛ**/ ቀን ተገናኝተው ይጨፍራሉ  (አባሪ 6 ይመልከቱ)

ከላይ የተገለጹትን የቋንቋ አጠቃቀም ትንተናዎችን ከዚህ በታች በሠንጠረዥ አምስት ጠቅለል አርገን እናያለን፡፡

ሠንጠረዥ 5.በቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ምድብ የተፈጸሙ የስህተት ዓይነቶች መግለጫ

| የስህተት አይነት ምድቦች | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት ብዛት በቁጥር | የስህተት ብዛት በመቶኛ | አማካይ ስህተት | የስህት ድግግሞሽ | የስህተት ብዛት በቁጥር | የስህተት ብዛት በመቶኛ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተት ብዛት በቁጥር | የስህተት ብዛት በመቶኛ | አማካይ ስህተት | የስህተት ድግግሞሽ |
| የሆሄያት ስህተት | 863 | 8.3 | 7.19 | 8.3 | 663 | 5.6 | 5.53 | 5.6 | 1526 | 6.85 | 12..72 | 6.85 |
| የሆሄያት ግድፈት | 731 | 7 | 6.09 | 7 | 518 | 4.38 | 4.32 | 4.38 | 1249 | 5.61 | 10.41 | 5.61 |
| ያልተለዩ ስህተቶች | 387 | 3.71 | 3.23 | 3.71 | 325 | 2.75 | 2.71 | 2.75 | 712 | 3.2 | 5.93 | 3.2 |
| የቃላት ድግሞሽ | 275 | 2.63 | 2.29 | 2.63 | 235 | 1.99 | 1.96 | 1.99 | 510 | 2.3 | 4.25 | 2.3 |
| ጠቅላላ ድምር | 2256 | 21.64 | 18.8 | 21.64 | 1741 | 14.72 | 14.52 | 14.72 | 3997 | 17.96 | 33.31 | 17.96 |

### 4.2.2.የቋንቋ አወቃቀር ስህተት

ታላሚ ተማሪዎች ከአፍ-መፍቻ ቋንቋቸው በተጨማሪ የሚማሩትን ቋንቋ ሰዋስዋዊ አወቃቀር ሥርዓት ካለማወቅ የተነሳ ስህተት ሲፈጽሙ ይስተውላሉ፡፡በዚህ ስህተት ስር አራት ንዑሳን የስህትት ዓይነቶች ይገኛሉ፡፡እነርሱም የዓረፍተ ነገርስምምነት (በዓረፍተ ነገር ውስጥ የቁጥር፣የፆታ እና የመደብ አለመስማማት )፣የመስተዋድድ አገባብ ስህተት፣የተሳቢ አገባብ ስህተት እና የአያያዦች አጠቃቀም ስህተቶች ናቸው፡፡ከአጠቃላይ ስህተቶች----ውስጥ 1901 ስህተቶች የንቋ አወቃቀር ስህተቶች ናቸው፡፡በዚህ አብይ የስህተት ምድብ ወስጥ ያሉትን አራት ንዑሳን ስህተቶች እንደሚከተለው በዝርዝር እናያለን፡፡

#### 4.2.2.1. በዓረፍተነገር ውስጥ የባለቤት እና ግስ አለመስማማት ስህተት

በዓረፍተነገር ውስጥ የባለቤት እና ግስ ያለመስማማት ስህተት ከሚፈጥሩት ውስጥ የፆታ፣የቁጥር እና የመደብ አለመስማማት ሲሆን እነርሱም የባለቤት ማሰሪያ አንቀጽ እና ተሰቢ አለመስማማትን ይጠቁማሉ፡፡በዚህ ንዐስ የስህተት ስር ሶስት የስህተት ዓይነቶች ተመድበዋል እነርሱም የፆታ፣ የመደብ እና የቁጥር አለመስማማት ናቸው፡፡ ተማሪዎቹ በጻፉት ድርሰት ውስጥም የተገኙት ስህተቶች ይህንኑ እንደሚጠቁሙ ዝርዝሩን ምሳሌ እየጠቀስን ከዚህ በታች እንደየቅደም ተከተላቸው እናያለን፡፡

- **የቁጥር በዓረፍተነገር ውስጥ አለመስማማት**

በዓረፍተነገር አወቃቀር ውስጥ የቁጥር አለመስማማት የባለቤት እና የግስ ትርጉም ያዛባል፡፡ አንደኛው በነጠላ የቀረው በብዙ የሚገለጽ ከሆነ የተፋለሰ ዓረፍተነገር ነው የሚሆነው፡፡

ስለ ሲዳማ ‹‹ባህላዊ ዳኝነት››ተማሪዎቹ ከጻፉት ድርሰት ለአብነት የተወሰደ ፡-

ሴዎች ኬቴጣላ ሺማጊሌዎች ያስታሪቃል…

በሽንገ አንድ ሴው ሌሺማጊሌ ቆሞ ዪናገራሉ…

ሲታረቁ ያጠፉ ሰዎች ከብት ይቀጣል…

በመጀመሪያው ዓረፍተነገር ሰዎች(የዓረፍተነገሩባለቤት) የብዙ ቁጥር መግለጫ የሆነቸውን ጥገኛ ምዕላድ ወይም ቅጥያ ሰው-ኦች /-ኦችች/ን እናገኛለን፤በመቀጠል **(ተጣላ)** የሚለው ግስ 3ኛ መደብ ነጠላ ቁጥር የሚያመለክት ግስ ነው፤አሁንም በመቀጠል ሽማግሌዎች እና ያስታርቃል የሚለው ከመጀመሪያው ጋር ተመሳሳይ ስህተት ነው፤በሁለቱም ቦታ የምናየው ነጠላ እና ብዙ ቁጥር በሆኑ ስህተቶች የባለቤት፣ የተሳቢ እና የግስ አለመስማማት ነው፡፡

ሁለተኛውን ምሳሌ ስናይ አንድ ሰው በማለት የተናጋሪውን ብዛት በነጠላ መጥኖታል ፤ነገር ግን ተናጋሪውን አንድን ሰው የሚገልጽ ግስ ወይም ማሰሪያ አንቀጽ መሆን ሲገባ/ ይናገራሉ/ በሚል 3ኛ መደብ ብዙ ቁጥር ተገልጿል፤በዚህ አገላለጽም ሁለት የተለያዩ ነገሮችን ወይም የቁጥር ልዩነቶችን እናያለን የነጠላ እና የብዙ ቁጥር በመሆኑም የተዛባ የባለቤትና የግስ አወቃቀር እናገኛለን፡፡በ3ኛው ምሳሌ ላይም የምናየው መድገም ካልሆነ በስተቀር ተመሳሳይ ስህተት ነው፡፡(አባሪ 1 እና 5 ይመልከቱ)

- **የፆታ እና የመደብ ስህተት**

ዓረፍተነገር ከቁጥር በተጨማሪ የፆታ እና የመደብ ስምምነት ሲኖራቸው የባለቤት እና ግስ ትስስር ይታይባቸዋል፡፡ነገር ግን ተጠኚ ተማሪዎች በጻፉት ድርሰት ውስጥ እነኚህን ጉድለቶች እናገኛለን፡፡ለአብነት ተማሪዎች ስለ ሲዳማ‹‹ ቤት አሰራር››ከጻፉት ድርሰት የሚከተሉትን እናያለን፡፡

<u>ቤ</u>ሲዳማ ቤት ሲሰራ ወንዱ ጌሜድ መጎተቻ ታቀርባለች…

ሊጃጌረድ <u>ሌ</u>ጪቃ ውሀ ይቀዳል…

ዌንዱ ጣሪያ ላይ ሳር ቲኬድናለች…

ሁላችንም <u>ከ</u>ጫካ ቱሼ ዌይም ማሰሪያ ፌልገን አምጥተዋል…

/ጎረቤቶቹ/ ቤቱ ሲሰራ ቡርሳሜ አምጥተን/--ን/ ሰጥተ/ና/ል/

በነኚህ ዓረፍተ ነገሮች ላይ ሁለት ነገሮችን እናያለን፡፡የመጀመሪያዎቹ ሶስቱ ላይ የፆታ አለመስማማት ስህተት ሲሆኑ ቀጥሎ ያሉት የመደብ አለመስማማትን የሚያሳዩ ናቸው፡፡የመጀመሪያውን ምሳሌ ቤሲዳማ ቤት ሲሰራ ወንዱ ጌሜድ መጎተቻ ታቀርባለች…የሚለውን ብናይ የአረፍተነገሩ ባለቤት /ወንዱ/ በተባዕት የተገለጸ ሲሆን ግሱ ግን እንስት አመልካች /ታቀርባለች/ ነው፡፡በዚህ ዓረፍተነገር ግስ ላይ የምትገኘዋ /-ኧች/ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር እንስት አመልካች ቅጥያ ነች የምትገልጸውም ይህንኑ ነው ይሁን እንጂ ባለቤት ተባዕትን አትገልጽም፡፡ ሁለተኛው ምሳሌ ላይ /ልጃገረድ /ለጭቃ ውሀ /ይቀዳል/፤በዚህኛው ደግሞ የዓረፍተነገሩ ባለቤት እንስት ስትሆን ማሰሪያ አንቀጹ ተባዕት ነው፡፡/ይ-/ ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባዕት አመልካች መነሻ ቅጥያ ነች በመሆኗም ለዕንስት ባለቤት አትሆንም፡፡ከዚህ የተነሳ ዓረፍተነገሩ ላይ የባለቤት እና የግስ አለመስማማት ታይቷል፡፡መንስዔው ደግሞ የፆታ አለመስማማት ነው፡፡ሶስተኛውም ምሳሌ መድገም ካልሆነ በስተቀር ስህተቱ ተመሳሳይ ነው፡፡

ወደአማርኛው ቋንቋ ስርአተ አጻጻፍ ሲመለስ ወይም ሲስተካከል፦

በሲዳማ ቤት ሲሰራ ወንዱ ገመድ መጎተቻ ያቀርባል...

ልጃገረድ ለጭቃ ውሀ ትቀዳለች...

ወንዱ ጣሪያ ላይ ሳር ይከድናል... የሚል የሆናል ( ተጨማሪ አባሪ 2 እና 7 ይመልከቱ)

በመቀጠል የምናየው ሁለቱ ምሳሌዎች በዓረፍተነገር ውስጥ የመደብ አለመስማማት ነው። የመጀመሪያውን ምሳሌ እንይ ፦

/ሁላችንም/ ከጫካ ቱሼ ዌይም ማሰሪያ ፈልገን/ አምጥተዋል/...የዚህ ዓረፍተነገር ባለቤት በሁላችን የተገለጸው ተውላጠ ስም /እኛ/ይሆናል ነገርግን በግሱ ላይ የምትገኘዋ መድረሻ ቅጥያ/-ው/ የምታመለክተው 3ኛ መደብ ብዙ ቁጥርን ነው በመሆኑም የባለቤት እና የግስ አለመጣጣም ታይቷል።

/ጎረቤቶቹ/ ቤቱ ሲሰራ ቡርሳሜ አምጥተን/--ን/ ሰጥተ/ና/ል/= ሰጥተ /--ን/ በዚህ አረፍተነገር ላይ ያለው ባለቤት በ /--ኦችቸ/ እና /--ኡ/የተጠቆመው 3ኛ መደብ ብዙ ቁጥር ሲሆን በመጀመሪያው ግስ ላይ የምናገኘው /--ን/ አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር ባለቤት የሚጠቁመን የባለቤት አጻፉ ነው፤በመጠረሻ ላይ የሚገኘውም ሰጥተናል /-ን/ አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር አመልካች ቅጥያ ነች በመሆኑም የዚህ ዓረፍተ ነገር ባለቤት 3ኛ መደብ ብዙ ቁጥር ከሆነ ግሱም እሄንኑ የሚገልጽ ሰጡ የሚል መሆን ነበረበት ግን አይደለም፤የሆነው ግን አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር አመልካች ቅጥያ /--ን/ ነች ዓረፍተነገሩ ውስብስብ ቢሆንም የባለቤትና የግስ መለያየትን እንደዚህ ማሳየት አልነበረበትም፤በመሆኑም የዓረፍተነገሩ ባለቤትና ግስ ወይም ማሰሪያ አንቀፆች አልተስማሙም ከዚህ የተነሳ የመደብ ስህተቱ በዐረፍተነገሩ ውስጥ የባለቤት እና የግስ አለመስማማትን ፈጥሯል።ስለዚህ በአማርኛው ቋንቋ ስርአተ-አጻጻፍ ሲስተካከል እንደሚከተለው ይሆናል።

ሁላችንም ከጫካ ቱሼ ወይም ማሰሪያ ፈልገን አምጥተናል...

ጎረቤቶቹ ቤቱ ሲሰራ ቡርሳሜ አምጥተው ሰጥተዋል የሚል ይሆናል። (አባሪ 7 እና 2 ይመልከቱ)

ከምሳሌዎቹ አንጻር የስህተቶቹ መንስኤ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መዋቅራዊ ስርአት ሊሆን እንደሚችል ነው።

#### 4.2.1.2.የመስተዋድድ አገባብ ስህተት

ተማሪዎች በጻፉት ድረሰት ውስጥ በቋንቋ አወቃቀር ስህተት ስር በሁለተኛ ደረጃ የምናገኘው የመስተዋድድ አገባብ ስህተት ነው፡፡በዚህ የስህተት ምድብ ስር የተከሰቱት ስህተቶች መስተዋድድ መግባት በሚያስፈልገው ቦታ ላይ አለማስገባትና መግባት በማያስፈልገው ቦታ ላይ በማስገባት የሚፈጠር ስህተት ነው፡፡በቋንቋ አወቃቀር ስህተት ምድብ ስር ከተቆጠሩት 1901 ስህተቶች ውስጥ 438 (1.97) ስህተቶች ሲገኙ አማካይ ስህተት 1.83 እና የስህተት ድግግሞሹ 1.97 ሆኗል፡፡

ይህን ክስተት ተማሪዎቹ ከጻፉት ‹‹የሲዳማ ቤት አሰራር››ከሚለው ድርሰት ለአብነት እንደሚከተለው እናያለን፡- የመስተዋድድ አገባብ ስህተቱ በቅንፍ( ) የተገለጸው ነው፡፡

ዬቤት ጫፍ ( )ጋጥ ማስቀመጫ ዬሰራል…

ኬሚሶሶ ማቆም ጀሚሮ ( )ሳር መክደን ሴቶች ያጊዛሉ…

ቤሲዳማ ሴቶች ( )ዌንዶች ቤላይ ዬሰራሉ…

ቤሲዳማ ቤት ሲሰራ (ቤ)ወጣቶች ጊራጊዳ ዬፌልጣሉ…

ዬሲዳማ ቤት ኪዳን (ቤ)ሜሬት ዲረስ ነው ዬሚሰራው…

ቤቱ ቴሰራቶ ሲያሊቅ ( ከ)ሺማጊሎች ዬመረቃል… እነኚህን ስህተቶች እንደመስተዋድዱ አገባብ ሁኔታ (ቦታ) ለሁለት ከፍለን እንየው፡-

#### ሀ.መግባት በሚገባቸው ቦታ ላይ ሳይገቡ በመቅረታቸው የተፈጠሩ ስህተቶችን እናያለን

ዬቤት ጫፍ ( )ጋጥ ማስቀመጫ ዬሰራል…በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ በቅንፍ ( )በተመለከተበት ቦታ ላይ /ከ/ ቢገባ ኖሮ ትክክል ነበር ነገር ግን አልሆነም ፤ ኬሚሶሶ ማቆም ጀሚሮ ( )ሳር መክደን ሴቶች ያጊዛሉ…በዚህኛው ዓረፍተነገር በቅንፉ( ) ቦታ ላይ /እስከ/ቢገባ ኖሮ ትክክል ነበር ግን አልተደረገም፤ቤሲዳማ ሴቶች ( )ዌንዶች ቤላይ ዬሰራሉ…በዚህኛውም ዓረፍተነገር በቅንፉ( )ቦታ /ከ/ቢገባ ኖሮ ዓረፍተነገሩ ትክክል ነበር ፤በአጠቃላይ ከላይ ያየናቸው ዓረፍተነገሮች ላይ ያየነው መስተዋድዶቹ መግባት በሚገባቸው ቦታ ላይ ሳይገቡ በመቅረታቸው በዓረፍተነገሩ ላይ ስህተት ተከስቷል፡፡በአማርኛው ቋንቋስርአተ-አጻጻፍ ሲስተካከል እንደሚከተለው ይሆል፡-

የቤት ጫፍ ከጋጥ ማስቀመጫ ይሰራል…

ከምሶሶ ማቆም ጀምሮ እስከ ሳር መክደን ሴቶች ያግዛሉ…

በሲዳማ ሴቶች ከወንዶች በላይ ይሰራሉ…የሚል ይሆናል፡፡

**ለ.መስተዋድዶቹ መግባት በማይገባቸው ቦታ ላይ በመግባት የተፈጠሩትን ስህተቶች እናያለን**

ቤሲዳማ ቤት ሲሰራ (ቤ)ወጣቶች ጊሪጊዳ ዪፌልጣሉ…በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ በቅንፍ ውስጥ ያለው መስተዋድድ ያለቦታ በመግባቱ ዓረፍተ ነገሩ ትክክል አይደለም በቅንፍ ውስጥ ያለው /በ/ሲወገድ ትክክል ይሆናል፤በመቀጠል ያለው ዩሲዳማ ቤት ኪዳን (ቤ)ሜሬት ዲረስ ነው ዩሚሰራው…ይህ  የሚያመለክተን በቅንፍ ውስጥ ያለው መስተዋድ የዓረፍተነገሩን ትርጉም አዛብቷል ዓረፍተነገሩ ትርጉም የሚሰጠው በቅንፉ ቦታ ላይ /እስከ/ቢገባ ኖሮ ትክክለኛ ትርጉም ይሰጠን ነበር፤በመጨረሻላይ ያለው ምሳሌ ቤቱ ቴሰራቶ ሲያሊቅ (ከ)ሺማጊሎች ዩመረቃል… በዚህኛውም ዓረፍተነገር ላይ በቅንፉ( )ውሰጥ የገባው መስተዋድድ ቦታው አይደለም በመሆኑም የዓረፍተነገር ስህተት ክስተት ታይቷል፡፡ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱት የመስተዋድድ አገባብ ስህተቶች የተገለጹት ወይም የተተነተኑት ተጠኚ ተማሪዎቹ ከጻፉት ዐውድ አንፃር መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል፡፡ከአረፍተ ነገሩ አውድ አንጻር ተስተካክሎ ሲጻፍ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

በሲዳማ ቤት ሲሰራ ወጣቶች ግርግዳ ይፈልጣሉ…

የሲዳማ ቤት ኪዳን ሜሬት ድረስ ነው የሚሰራው…

ቤቱ ተሰርቶ ሲያሊቅ ሽማግሌዎች ይመርቃሉ… (አባሪ 2 እና 7 ይመልከቱ)

**4.2..1.3.የተሳቢ አገባብ ስህተት**

በቋንቋ አወቃቀር ስህተት ስር በሶስተኝነት የተቆጠረው የተሳቢ አገባብ ስህተት ነው፡፡የተሳቢ አገባብ ስህተት በዓረፍተነገር ውስጥ መግባት በሚገባበት ቦታ ላይ ባለማስገባት  እናመግባት በማይገባበት ቦታ ላይ በማስገባት የሚፈጠር ስህተት ነው፡፡በአጠቃላይ በቋንቋ አወቃቀር ከተቆጠሩት ስህተቶች1901 ውስጥ 424 (1.9) ስህተት የተቆጠረው የተሳቢ አገባብ ስህተት ነው፤አማካይ ስህተት1.77ሲሆን 1.9ደግሞ የስህት ድግግሞሽ ነው፡፡በድርሰቶቹ ውስጥ የተገኙትን ስህተቶችን  ተማሪዎች ከጻፉት ‹‹የሲዳማ ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት›› ድርሰት ለአብነት እንደሚከተለው እናያለን፡-

ቤሲዳማ ጢል ሲፌጠር ሺማጊሌዎች ሰዎች( )ያስታሪቃሉ…
ባል ሚሲት( ) ያሌአጊባብ ኬዶቤዶቤ ቤኮርማ ዩቄጣል…
ዌላጅ ሊጆቹ( )ዩሚቀጣው ቂቤ ቤቴቀባ ሀለንጋ ኔው…

በሶስቱም ምሳሌዎች ላይ የምናየው በቅንፉ ውስጥ መግባት ሲገባው ያልገባ የዓረፍተነገር አካል እንዳለ ነው፤እሱም በዓረፍተነገር አወቃቀር የተሳቢ/--ን/ጉድለት ነው፡፡ በመሆኑም ዓረፍተነገሩ ላይ ስህተት ይታያል ፤ይህ ስህተት ትክክል የሚሆነው በቅንፉ ቦታ ላይ ተሳቢ አመልካች ቅጥያ/--ን /ስትገባ ነው፡፡ከአረፍተነገሩ አውድ አንጻር እንደሚከተለው ይስተካከላሉ፡-

በሲዳማ ጥል ሲፈጠር ሽማግሌዎች ሰዎችን ያስታሪቃሉ…
ባል ሚሲትን ያለአግባብ ከደበደበ በኮርማ ይቀጣል…
ወላጆች የሚቀጡት ቅቤ በተቀባ ሀለንጋ ነው… (አባሪ 1 እና 5 ይመልከቱ)

### 4.2.1.4.የአያያዥች አጠቃቀም ስህትት

በቋንቋ አወቃቀር ዓብይ የስህተት ስር ከተጠቀሱት ስህተቶች የመጨረሻውን የስህተት ቁጥር የያዘው የአያያዥች አጠቃቀም ስህተት ሲሆን በዚህ ምድብ ከተቆጠሩት 1901 ስህተቶች ውስጥ 341(1.53) የአያያዥች አጠቃቀም ስህተት ነው፡፡አማካይ ስህተት1.42 ሲሆን የስህተት ድግግሞሹ 1.53 ነው፡፡በተማሪዎቹ ድርሰት ውስጥ ስለ‹‹ሲዳማ በዓል ፊቼ ጨምበለላ››በጻፉት ውስጥ ከተከሰቱት ስህተቶች ለአብነት እንደሚከተለው እናያለን፡፡

በፊቼ ጨምበላላ ዌንዶች ( )ሴቶች አብረው ዩጨፊራሉ…

ሺማጊሌዎች ሌቢቻቸው ጋሻ ( )ጦር ይዘው ዩጨፍራሉ…

ዌጣቶች ( )ጎሮምሳዎቹ ዬሲጋ ኬብት አምጥተው በሺማጊሌ ዩሜረቃሉ…

በነኚህ ምሳሌዎች ውስጥ በቅንፍ የተጠቀሰው በዓረፍተነገሩ ውስጥ መግባት የሚገባው የዓረፍተነገር አካል ባለመግባቱ የተፈጠረውን ጉድለት ነው፡፡ስለዚህ ዓረፍተነገሩ ትክክል የሚሆነው (የሚስተካከለው) በመጀመሪያው እና በሚቀጥለው ዓረፍተነገር በቅንፉ ቦታ ላይ አያያዥ /እና/ሲገባ የዓረፍተነገሩ ትርጉም ወይም አወቃቀር ሙሉ ይሆናል፤የመጨረሳዓረፍተነገር ከመጀመሪያዎቹ በአያያዥ ዓይነቱ ይለያዩ እንጂ ተግባራቸው ተመሳሳይ ነው፤በመሆኑመረ በመጨረሳ ምሳሌ ቅንፍ ቦታ ላይ አያያዥ /ወይም/ሲገባ ዓረፍተነገሩ የተሟላ ትርጉም ይሰጣል፡፡ በመሆኑም ተስተካክሎ ሲጻፍ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

በፊቼ ጨምበላላ ወንዶች **እና** ሴቶች አብረው ይጨፍራሉ…
ሽማግሌዎች ለብቻቸው ጋሻ **እና** ጦር ይዘው ዩጨፍራሉ…
ወጣቶቹ **ወይም** ጎሮምሳዎቹ ዬሲጋ ኬብት አምጥተው በሺማጊሌ ዩሜረቃሉ…(አባሪ 6 ይመልከቱ)

**ሠንጠረዥ 6 .በቋንቋ አወቃቀር ስህተት ምድብ የተፈጸሙ የስህተት ዓይነቶች መግለጫ**

| | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት ብዛት በቁጥር | የስህተት ብ በመቶኛ | አማካይ ስ | የስህተ ድግግሞ | የስህተት ብዛትበቁጥ | የስህተት በመቶኛ | አማካይ ስ | የስህተት ድግግሞሽ | የስህተትብ በቁጥር | የስህትብ በመቶኛ | አማካይ | የስህተት ድግግሞሽ |
| የዓረፍተነገር ስምምነት | 384 | 3.68 | 3.2 | 3.68 | 314 | 2.65 | 2.62 | 2.65 | 698 | 3.13 | 2.91 | 3.13 |
| የመስተዋድድ አገባብ | 234 | 2.24 | 1.95 | 2.24 | 204 | 1.72 | 1.7 | 1.72 | 438 | 1.97 | 1.83 | 1.97 |
| የተሳቢ አገባብ | 215 | 2.1 | 1.79 | 2.1 | 209 | 1.77 | 1.74 | 1.77 | 424 | 1.9 | 1.77 | 1.9 |
| የአያያዦች አጠቃቀም | 177 | 1.7 | 1.48 | 1.7 | 164 | 1.39 | 1.37 | 1.39 | 341 | 1.53 | 1.42 | 1.53 |
| ድምር | 1010 | 9.72 | 8.42 | 9.72 | 891 | 7.53 | 7.43 | 7.53 | 1901 | 8.54 | 7.92 | 8.54 |

## 4.3.መመደብ ያልተቻሉ ስህተቶች

ተማሪዎች ከጻፉት ድርሰቶች ውስጥ ዝቅተኛ ቁጥር የያዙት የአብይ ስህተት ምድቦች ውስጥ መመደብ ያልተቻሉት ስህተቶች ናቸው፡፡ በዋናዋና የስህተት ምድቦች ሥር ከተቆጠሩት አጠቃላይ 7996 የስህተት መጠኖች ውስጥ 199(1.8) በዚሁ ስህተት የተቆጠሩ ናቸው፡፡አማካይህ ስህተቱ1.68 ሲሆን የስህተት ድግግሞሹ 1.82 ነው፡፡

ስለ‹‹ሲዳማ ቤት አሰራር ››እና ‹‹የሲዳማ ባህላዊ ዳኝነት ›› ከተጻፉት ድርሰቶች ውስጥ የተገኙትን መመደብ ያልተቻሉትን ስህተቶች ከዚህ በታች ለአብነት እናያለን፡-

ያማሰሬው ቤቀረጥነ…፣ያክይፉ ላሉ በመቀጠል…፣ቤመቀመለ …ሆዌ ሆንሳ ማለትም ቤቱን…በረ መሰት ማለት ነው…ቤቱን ማጠረ ማለት ነው..ሲጋል ቀረክ ነው… ቀረጥሃ ያዘጋጃሉ…ማለት በደዩን ይጭቃቅለ…ከዚየም በደየም..ይህደለ ብቀቅጥ መለ ቅጣቱ…ይህን ነወ ስህተት ከዚህ በታች ጠቅለል አርገን በሠንጠረዥ  እናያለን፡-በተጨማሪ (አባሪ 1፣2፣5 እና 7 ይመልከቱ)

**ሠንጠረዥ 7 መመደብ ያልተቻሉ ስህተቶችን  የሚያሳይ ጠቅለል ያለ መግለጫ**

| የስህተት ምድቦች | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የስህተት ብዛትበቁጥር | የስህተት በመቶኛ | አማካይ | የስህት ድግግሞ | የስህተት ብዛትበቁ | የስህተት በመቶኛ | አማካይ | የስህተት | የስህተት በቁጥር | የስህተት በመቶኛ | አማካይ ስ | የስህተት ሞሽ |
| መመደብ ያልቻሉ | 108 | 1.03 | 0.9 | 1.03 | 91 | .87 | .76 | .87 | 199 | 1.81 | 1.68 | 181. |

**ከላይ ለተገለጹት ስህተቶች ሁሉ በቀጥታ የስህተት መንስኤ ባይሆኑም ለስህተት መፈጸም ምክንያት የሆኑትን ከተማሪዎችና ከመምህራን የተገኙ ቃለመጠይቆችና የጽሁፍ መጠይቆችን ምላሾች እንደሚከተለው እናያለን፡-**

በቅድሚያ የተማሪዎችን ምላሽ ካየን በኋላ የመምህራንን በማስከተል እንደየአጠያየቃቸው ቅደም ተከተል እናያለን

ሰንጠረዥ 8፡ በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ትገኛል /ሽ/

| በአማርኛትምህርትክፍለጊዜበመማሪያክፍልውስጥት ገኛለህ /ሽ/ | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| ሀ/ሁልጊዜእገኛለሁ | 6 | 5.0 |
| ለ/አብዛኛውንጊዜእገኛለሁ | 7 | 65.0 |
| ሐ/በመጠኑእገኛለሁ | 26 | 21.7 |
| መ/አብዛኛውን ጊዜ አልገኝም | 78 | 65 |
| ሠ/በፍጹም አልገኝም | 3 | 2.5 |
| ድምር | 120 | 100.0 |

የዚህ መጠይቅ ዓላማ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለጊዜን አክብረው ወይም ጠብቀው ይማሩ እንደሆነ ለማጣራት እና ፍላጎታቸውንም ለማወቅ የተዘጋጀ ነው ፤በዚህም መሠረት እንደሚከተለው መልሰዋል፡- ሁልጊዜ እገኛለሁ6(5%) አብዛኛውን ጊዜእገኛለሁ 7(5.83%) በመጠኑ እገኛለሁ26(21%) አብዛኛውን ጊዜ አልገኝም 78(65%) በፍጹም አልገኝም 3(2.5%) መርጠዋል፤ ከምላሻቸው ተነስተን ጠቅለል አርገን ለሁለት ከፍለን እንኳ ብናይ አብላጫው ተማሪዎች የመማር ፍላጎት እንደሌላቸው እንረዳለን፤ከ120 ተማሪዎች እንኳ 78 (65%))በመማሪያ ክፍል ውስጥ አለመገኘታቸው ክፍለጊዜውን ለመማር ፍላጎት እንደሌላቸው አሳይተዋል፡፡

ሰንጠረዥ 9፡ በተራ ቁጥር አንድ ለቀረበው ጥያቄ መልስህ /ሽ ከሐ እስከ ሠ/ካሉት አንዱ ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው?

| . በተራ ቁጥር አንድ ለቀረበው ጥያቄ መልስህ /ሽ ከሐ እስከ ሠ/ካሉት አንዱ ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው? | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| ሀ/ አማርኛ ቋንቋ መማር ስለማልወድ | 72 | 60.0 |
| ለ/ከመምህሩ ጋር ስለማልስማማ | 8 | 6.67 |
| ሐ/አማርኛን ባልማረውም ማወቅ ስለምችል | 12 | 10 |
| መ/የትምህርቱ አቀራረብ ስለማያስደስት | 11 | 9.17 |
| ሠ/ትምህርቱ በጣም ስለሚከብደኝ | 7 | 5.83 |
| ድምር | 120 | 100.0 |

በእርግጥ የዚህ መጠይቅ ዓላማ የመጠይቅ አንድ ምላሽ አሉታዊ ከሆነ ምክንያቱን ለማወቅ ነበር፡፡በሆኑም አሉታዊ ሆኖ በመገኘቱ ምክንያቱን ዕንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡ አማርኛ ቋንቋ መማር ስለማልወድ 72(60%) ከመምህሩ ጋር ስለማልስማማ 8 (6.67%)አማርኛን

ባልማረውም ማወቅ ስለምችል 12(10%) የትምህርቱ አቀራረብ ስለማያስደስት 11(9.17%)ትምህርቱ በጣም ስለሚከብደኝ 7(5.83%) በማለት የየራሳቸውን ፍላጎት ገልጸዋል፡፡በዚህኛውም በምክንያት ፍለጋ ምላሽ የተረዳነው ተማሪዎቹ በመጠይቅ አንድ የመለሱትን ምላሽ ትክክለኛነት አረጋግጠዋል፡፡ሁለቱም ምላሾች የሚያረጋግጡልን በክፍል ውስጥ የማይገኙ እና የመማር ፍላጎት ከሌላቸው በአማርኛ ቋንቋ ላይ ያላቸው አሉታዊ ነገር በሚጽፉት ድርሰት ላይ የስህተት ችግር እንደሚፈጠር መገመቱ ምንም ጥርጥር አይኖረውም ፡፡እንዲያውም ለስህተቱ መንስዔ ዋናው በክፍል ውስጥ ተገኝተው አለመማራቸው እና ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ መሆን እንደሆነ እንገነዘባለን ፡፡

**ሰንጠረዥ 10፡ በመማሪያመጽሐፉውስጥአማርኛንየምትማረው /የምትማሪው/**

| .በመማሪያመጽሐፉውስጥአማርኛንየምትማረው /የምትማሪው/ | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| ሀ/ ሙሉበሙሉከመማሪያመጽሐፉነው | 69 | 57.5 |
| ለ/ በአብዛኛውከመማሪያመጽሐፉነው | 38 | 31.67 |
| ሐ/በመጠኑ ከመማሪያ መጽሀፉ ነው | 11 | 9.16 |
| መ/በአብዛኛው ከመማሪያ መጽሀፉ ውጪ ነው | 2 | 1.67 |
| ሠ/ሙሉ በሙሉ ከመማሪያ መጽሀፉ ውጪ ነው | 0 | 0 |
| ድምር | 120 | 100.0 |

አማርኛን የሚማሩት ወይም መምህራቸው የሚያስተምራቸው ማስተማሪያ መሳሪያውን ለማወቅ የተዘጋጀ መጠይቅ ነው፤ዓላማው ድርሰትን ስተምሯል ወይስ አላስተማረመረ የሚለውን ለማወቅ ቀጥታ ጥያቄ ሳይሆን በተዘዋሪ ለማወቅ የቀረበ ነው ሆኖም የተማሪዎቹ ምላሽ ሙሉበሙሉከመማሪያመጽሐፉነው69(57.5%) በአብዛኛውከመማሪያመጽሐፉነው 38(31.67%)በመጠኑ ከመማሪያ መጽሀፉ ነው11(9.16%) በአብዛኛው ከመማሪያ መጽሀፉ ውጪ ነው 2(1.67%) ሙሉ በሙሉ ከመማሪያ መጽሀፉ ውጪ ነው 0 በዚህ መጠይቅ ውስጥ መምህራን መማሪያ መጽሀፉን እንደሚያስተምሩ በአብላጫ ድምጽ (ሙሉበሙሉ ከመማሪያ መጽሐፉ ነው 69(57..5%) እና በአብዛኛው ከመማሪያ መጽሐፉ መሆኑን በ38(31.67%)) ተጠኝዎች ታይቷል፡፡

ሰንጠረዥ 11፡ ትምህርቱ በአብዛኛው የሚያተኩረው በየትኛው ይዘት ላይ ነው

| ትምህርቱበአብዛኛውየሚያተኩረውበየትኛውይዘትላይነው | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| ሀ/በአረፍተነገርአይነቶችአመሰራረትናአገነባብ | 62 | 51.67 |
| ለ/ስለድምፆችአፈጣጠርናአገነባብ | 30 | 25.0 |
| ሐ/ስለቃላትአመሰራረት | 18 | 15.0 |
| መ/ስለቃላትየተለያየፍቺ | 7 | 5.83 |
| ሠ/ስለ ቋንቋ የተለያዩ አጠቃቀሞች | 3 | 2.5 |
| ድምር | 120 | 100.0 |

የዚህ መጠይቅ ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርቱ በአብዛኛው የሚያተኩረው በየትኛው ይዘት ላይ እንደሆነ ለማረጋገጥ ስለሆነ ከመጠይቁ የምንረዳው በመማሪያው መጽሀፉ ውስጥ የጽህፈት ይዘቶች ስላሉ በተዘዋዋሪ ለመረዳት የተፈለገው አስተምረዋል ወይስ አላስተማሩም የሚለውን ነው፡፡በመሆኑም በተማሪዎቹ ምላሽ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የጽህፈት ይዘት የሆነውን በአረፍተነገርአይነቶችአመሰራረትናአገነባብ የሚለው በ62(51.67%) ተማሪዎች ተጠቅሷል፤ቀሪዎቹ ተመጣጣኝ ባይሆኑምስለድምፆች አፈጣጠርናአገነባብ30(25%)፣ ስለቃላት አመሰራረት 18(15%)፣ስለቃላት የተለያየ ፍቺ 7(5.83%) እና ስለ ቋንቋ የተለያዩ አጠቃቀሞች 3(2.5%)በማለት መልሰዋል ይሁን እንጂ ሁሉም ቢደመሩ (በአንድላይ) እንኳ በአረፍተነገር አይነቶች አመሰራረትና አገነባብ ያሉትን አይደርሱም ወይም ተበልጠዋል በመሆኑም ድርሰትን ለማጻፉ በሌላ ቀጥታ ጥያቄ እስከሚደረስ ድረስ ጽህፈትን እንደሚማሩ በአብዛኛው ተማሪዎች ተጠቁሟል፡፡

ሰንጠረዥ 12፡ በአማርኛስትጽፍ/ፊ/ በይበልጥየሚያስቸግርህ/ሽ/ክፍልየትኛውነው

| በአማርኛስትጽፍ/ፊ/ በይበልጥየሚያስቸግርህ/ሽ/ክፍል የትኛውነው | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| ሀ/በቃላትድምጾችን በተገቢው ፊደል ወክሎ አለ መጻፍ | 12 | 10 |
| ለ/መደብአመልካችቅጥያዎችበትክክል አለመጻፍ | 26 | 21.67 |
| ሐ/ተገቢውንቃልበተገቢውቦታ ተጠቅሞአለመጻፍ | 6 | 5 |
| መ/ሀሳብንትክክልአቀናብሮመፃፍ | 13 | 10.83 |
| ሠ/ከላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች ሁሉ | 63 | 52.5 |
| ድምር | 120 | 100.0 |

የዚህ መጠይቅ ዓላማ ተማሪዎቹ በአማርኛ ሲጽፉ በይበልጥ የሚያስቸግራቸው የትኛው የጽህፈት ክንውን እንደሆነ ለመገንዘብ የቀረበ ጥያቄ ነው፡፡በዚህ መሠረት የ120 ተጠኚ ተማሪዎች ምላሽ እንደሚከተለው እናያለን፡-ከ120 ተጠኚዎች በቃላትድምጾችን በተገቢው ፊደል ወክሎ መጻፍ 12(10%)መደብአመልካችቅጥያዎችበትክክል አለመጻፍ 26(21.67%)ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ ተጠቅሞ አለመጻፍ 6(5% )ሀሳብን በትክክል አቀናብሮ መፃፍ 13(10.83% ) ከላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች ሁሉ ያስቸግረኛል 63 (52.5% )የሚለውን አማራጮች መርጠዋል ፤ይሁን እንጂ ከተጠኚዎች ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑቱ ወይም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች የሁሉም ችግር ወይም በቃላት ድምጾችን በተገቢው ፊደል ወክሎ አለመጻፍ ፣ መደብ አመልካች ቅጥያዎችን በትክክል አለመጻፍ፣ ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ ተጠቅሞ አለመጻፍ እና ሀሳብን በትክክል አቀናብሮ አለመጻፍ ችግር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 13 አማርኛመምህራችሁጽህፈትንለማስተማርበመማሪያመጽሀፉከቀረቡመልመጃዎችበተጨ ማሪከ መጽሐፍ፣ከመጽሄት፣ከጋዜጦችአንብባችሁወይምሰዎችንጠይቃችሁየተረዳችሁትንጽፋችሁእንድ ትመጡያደርጋሉ፡፡**

| አማርኛመምህራችሁጽህፈትንለማተማርበመማሪያመጽሀፉከቀረቡ መልመጃዎችበተጨማሪከመጽሐፍ፣ከመጽሄት፣ከጋዜጦችአንብባች ሁወይምሰዎችንጠይቃችሁየተረዳችሁትንጽፋችሁእንድትመጡያደ ርጋሉ | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| ሀ/ሁልጊዜያደርጋሉ | 0 | 0 |
| ለ/አብዛኛውንጊዜያደርጋሉ | 2 | 1.66 |
| ሐ/በመጠኑያደርጋሉ | 12 | 10 |
| መ/በእዛኛውንጊዜአያደርጉም | 40 | 33.33 |
| ሠ/ በፍፁምአድርገውአያውቁም | 66 | 55.0 |
| ድምር | 120 | 100.0 |

አማርኛ መምህራችሁ ጽህፈትን ለማስተማር በመማሪያ መጽሀፉ ከቀረቡ መልመጃዎች በተጨማሪ ከመጽሐፍ፣ ከመጽሄት፣ ከጋዜጦች አንብባችሁ ወይም ሰዎችን ጠይቃችሁ የተረዳችሁትን ጽፋችሁ እንድትመጡ ያደርጋሉ የሚለው የመጠይቁ ዓላማ ጽህፈትን በተለያዩ ርዕሶች ከተለያዩ ጽሁፎች ተረድተው እንዲጽፉ እንደ ሚያደርጉ ለመረዳት ነው፤ሆኖም የተማሪዎቹ ምላሽ በፍፁምአድርገውም አያውቁም ያሉት 66 ተማሪዎች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ሁልጊዜያደርጋሉ ምንም፣አብዛኛውን ጊዜ ያደርጋሉ2፣በመጠኑ ያደርጋሉ 2 እና በእዛኛውን ጊዜ አያደርጉም 40በማለት መልሰዋል፤አብዛኛውን

ጊዜ አያደርጉም  እና በፍፁም አድርገው አያውቁም የሚሉት ተቀራራቢ መልሶች በመሆናቸው ስናጠቃልለው አማርኛ መምህራችሁ ጽህፈትን ለማስተማር በመማሪያ መጽሀፉ ከቀረቡ መልመጃዎች በተጨማሪ ከመጽሐፍ፣ ከመጽሄት፣ ከጋዜጦች አንብባችሁ ወይም ሰዎችን ጠይቃችሁ የተረዳችሁትን ጽፋችሁ እንድትመጡ ያደርጋሉ የሚለው እንዳልተደረገ ወይም እንዳልተሰራ እንገነዘባለን፡፡

**ሰንጠረዥ 14: መምህራችሁበትምህርትቤታችሁለተቋቋሙየስነ-ጽሁፍናድራማወይምሚኒ-ሚዲያክበባትስነ-ጽሁፎችንወይምዘገባዎችንእንድታቀርቡያበረቷታቷችኋል**

| መምህራችሁበትምህርትቤታችሁለተቋቋሙየስነ-ጽሁፍናድራማወይምሚኒ-ሚዲያክበባትስነ-ጽሁፎችንወይምዘገባዎችንእንድታቀርቡያበረቷቷችኋል | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| ሀ/ዘወትርያበረታታሉ | 18 | 15.0 |
| ለ/አብዛኛውጊዜያበረታታሉ | 7 | 5.83 |
| ሐ/ በመጠኑያበረታታሉ | 20 | 16.66 |
| መ/ አልፎአልፎያበረታታሉ | 15 | 12.5 |
| ሠ/ በፍፁምአያበረታቱም | 60 | 50 |
| ድምር | 120 | 100.0 |

የዚህ መጠይቅ ዓላማ መምህራን በትምህርት ቤት በተቋቋመው የስነ-ጽሁፍና ድራማ ወይም ሚኒ-ሚዲያ ክበባት ስነ-ጽሁፎችን ወይም ዘገባዎችን እንዲያቀርቡ ያደረጉት ነገር (ሥራ )እንዳለ ለማወቅ ነበር፤ሆኖም የተመለሰው መልስ በአብዛኛው ተጠኚዎች 60 (50%)ተማሪዎች  አሉታዊ ምላሽ ነው ቀሪዎቹ የመለሱት ምላሽ ዘወትርያበረታታሉ 18(15%)አብዛኛውጊዜያበረታታሉ7(5.83%)

በመጠኑያበረታታሉ 20(16.66%) እና አልፎ አልፎ ያበረታታሉ 15(12.5%) በሚል ጠቁመዋል፤በጽህፈት ትምህርት ተጨማሪ የጽህፈት ትምህርት እንደማይሰጡ ከምላሹ እንረዳለን፡፡

ሰንጠረዥ 15፡ መምህራችሁ በጽሁፍ የሚመለስ የክፍል ወይም የቤትስራይሰጧችኋል

| መምህራችሁበጽሁፍየሚመለስየክፍልወይም የቤትስራይሰጧችኋል | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| ሀ /ሁልጊዜይሰጣሉ | 7 | 5.83 |
| ለ /አብዛኛውንጊዜይሰጣሉ | 34 | 28.33 |
| ሐ/ በመጠኑይሰጣሉ | 63 | 2.5 |
| መ/ አብዛኛውንጊዜአይሰጡም | 11 | 9.16 |
| ሠ/በፍፁምአይሰጡንም | 5 | 4.16 |
| ድምር | 120 | 100.0 |

የዚህ መጠይቅ ዓላማ መምህራን በጽሁፍ የሚመለስ የክፍል ወይም የቤትስራ እንደሚሰጡ ለማወቅ ሆኖ ድርሰት ደግሞ የጽሁፍ አካል እንደመሆኑ መጠን ለጽህፈት ልምምድ ምን ያህል ትኩረት እንደተሰጠ ለመገንዘብ የቀረበ ነው፤ከምላሹ የምንረዳው ግን ሁልጊዜይሰጣሉ7(5.83%)፣አብዛኛውን ጊዜ ይሰጣሉ 34(28.33%)፣በመጠኑ ይሰጣሉ 63(2.5%)አብዛኛውን ጊዜ አይሰጡም11(9.16%)እና በፍፁምአይሰጡንም 5(4.16%) ማለት መልሰዋል፡፡ከምላሹ የምንረዳው ግን በመጠኑ እንደሚሰጥ ካሉት ምላሾች አብዛኛውን ክፍል የያዘ በመሆኑ ለጽህፈት ልምምዱ በቂ ትኩረት እንዳልተሰጠ ነው፡፡

ሰንጠረዥ 16፡ በመምህራችሁየሚሰጧችሁየጽሁፍመልመጃዎችበአብዛኛውየሚያተኩሩት፣

| መምህራችሁየሚሰጧችሁየጽሁፍመልመጃዎችበአብዛኛውየሚያተኩሩት | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| ሀ/በቃላትአረፍተነገርመስራት | 78 | 65.0 |
| ለ/ደብዳቤወይምዘገባመፃፍ | 28 | 23.33 |
| ሐ/ረጅምጽሁፍማሳጠርወይምአጭርጽሁፍመሳጠር | 12 | 10.0 |
| መ/በተመረጡርዕሶችላይልቦለዶችንወይምኢልቦለዶችንመፃፍ | 2 | 1.67 |
| ድምር | 120 | 100.0 |

በመምህራችሁየሚሰጧችሁየጽሁፍመልመጃዎችበአብዛኛውየሚያተኩሩት ተብለው የተጠየቁት ዓላማው መምህራን በጽሁፍ መለማመጃ የሚያተኩሩት ምን በማሰራት እንደሆነ ለይቶ ለማወቅ ነው፡፡ከዚህ አንጻር የተማሪዎቹ ምላሽ በቃላትአረፍተነገርመስራት 78(68%)፣ ደብዳቤወይም ዘገባ መፃፍ 28(23.33%)፣ረጅምጽሁፍማሳጠርወይምአጭርጽሁፍመሳጠር 12(10%) እና በተመረጡ ርዕሶች ላይ ልቦለዶችን ወይም ኢልቦለዶችን መፃፍ 2 (1.67%)ከምላሹ የምንረዳው ትኩረት የተሰጠው በቃላት አረፍተ ነገር መስራት በ78(65) ተማሪዎች መጠቆሙ ትኩረት እየተደረገ ያለው በቃላት አረፍተ ነገርመስራት እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ቀሪዎቹ ቢደመሩ እንኳ ከግማሽ በታች በመሆናቸው ምላሹ በአብዛኛው ተማሪዎች ምርጫ ላይ አነጣጥሯል፡፡

**ሰንጠረዥ 17፡ መምህራችሁበክፍልምሆነበቤትየሚሰሩየጽሁፍ/ድርሰት/መልመጃዎችንያርማሉ**

| መምህራችሁበክፍልምሆነበቤትየሚሰሩየጽሁፍ/ድርሰት/መልመጃዎችንያርማሉ | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| ሀ/ ሁልጊዜያርማሉ | 6 | 5.0 |
| ለ/አብዛኛውጊዜያርማሉ | 6 | 5.0 |
| ሐ/ በመጠኑያርማሉ | 54 | 45.0 |
| መ/ አልፎአልፎያርማሉ | 48 | 40.0 |
| ሠ/በፍፁምአርመውአያውቁም | 6 | 5.0 |
| ድምር | 120 | 100.0 |

የዚህ መጠይቅ ዓላማ መምህራን በክፍልምሆነ በቤት የሚሰሩ የጽሁፍ /ድርሰት/ መልመጃዎችን ማረም አለማረማቸውን ለማረጋገጥ ነው፡፡በመሆኑም የተማሪዎችን ምላሽ እንደሚከተለው እናያለን፡-ሁልጊዜ ያርማሉ6(5%)፣አብዛኛው ጊዜ ያርማሉ 6(5%)፣ በመጠኑ ያርማሉ 54(45%)፣አልፎ አልፎ ያርማሉ 48(40%) እና በፍፁም አርመው አያውቁም 6(5%) ብለው ጠቁመዋል፡፡ ከተማሪዎቹ ምላሽ የምንረዳው በመጠኑ ያርማሉ 54 እና አልፎ አልፎ ያርማሉ ያሉት 48 ተማሪዎች መምህራን የተማሪዎቹን ጽሁፍ ወይም ድርሰት በትክክል ተከታትለው እንደማያርሙት ነው፡፡መምህራን አረመው ስህተትን የማይጠቁሙ ከሆነ ተማሪዎች ስህተት እየፈጸሙ ነው የሚሄዱት፡፡በመሆኑም ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የስህተት መንስዔ ሊሆን እንደሚችል እንረዳለን፡፡

**ሰንጠረዥ 18፡ አንተ (አንቺ) ለክፍልስራወይምለቤትስራየሚሰጣችሁንየጽሁፍ/የድርስት/ መልመጃዎችትሰራለህ/ሽ/**

| አንተ (አንቺ) ለክፍልስራወይምለቤትስራየሚሰጣችሁንየጽሁፍ /የድርስት/ መልመጃዎችትሰራለህ/ሽ/ | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| ሀ/ሁልጊዜእሰራለሁ | 6 | 5.0 |
| ለ/አብዛኛውንጊዜእሰራለሁ | 8 | 6.66 |
| ሐ/ በመጠኑእሰራለሁ | 11 | 9.16 |
| መ/ አልፎአልፎእሰራለሁ | 41 | 34.16 |
| ሠ/ ሰርቼአላውቅም | 54 | 45.0 |
| ድምር | 120 | 100.0 |

ይህ መጠይቅ ሲጠየቅ ዓላማው ለክፍል ስራ ወይም ለቤት ስራ የሚሰጠውን የጽሁፍ/ የድርስት/ መልመጃዎች ተማሪዎቹ ይሰሩ እንደሆነ ለማረጋገጥ ነው። በመሆኑም ምላሻቸውን አንድ በአንድ ስናይ እንደሚከተለው መልሰዋል።ሁልጊዜእሰራለሁ 6(5%)፣አብዛኛውን ጊዜ እሰራለሁ8(6.67%)፣በመጠኑእሰራለሁ11(9.16)፣ አልፎአልፎእሰራለሁ 41(34.16%) እና ሰርቼአላውቅም 54(45%) መልሰዋል አብዛኛው ተማሪዎች ድርሰቶችን እንደማይጽፉ ጠቁመዋል ፤በመጠኑ እሰራለሁ ካሉት እንኳ በግማሽ ብንወስድ እና አናውቅም ከሚሉት ጋር ደብለን ብናይ አብዛኛዎቹ የመለሱት አሉታዊ ምላሽ ነው ።

**ሰንጠረዥ 19፡ በተራቁጥርአስራአንድለቀረበውጥያቄመልስህ/ሽ/ ከ ,ሐ, እስከ,ሠ, ካሉትአንዱከሆነምክንያቱምንይመስልሃል/ሻል**

| በተራቁጥርአስራአንድለቀረበውጥያቄመልስህ/ሽ/ ከ ,ሐ, እስከ,ሠ, ካሉትአንዱከሆነምክንያቱምንይመስልሃል/ሻል | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| ሀ/ የየክፍልም ሆነየቤት ስራ መስራት ስለማልወድ | 55 | 45.83 |
| ለ/ድርሰትመፃፍስለሚከብደኝ | 47 | 39.17 |
| ሐ/ሰርቼ ብመጣም የማገኘው ጥቅም ስለሌለ | 6 | 5 |
| መ/መምህሩየሚሰጧቸውንመልመጃዎችስለማያርሙ | 12 | 10 |
| ድምር | 120 | 100.0 |

የመጠይቅ 11 ዓላማ የነበረው ለክፍል ስራ ወይም ለቤት ስራ የሚሰጠውን የጽሁፍ/ የድርስት/ መልመጃዎች ተማሪዎቹ ይሰሩ እንደሆነ ለማረጋገጥ ነበር።የዚህ መጠይቅ ምላሽ አሉታዊ

በመሆኑ ምክንያቱን ለማወቅ የተጠየቀ ነው፤ በመሆኑም ምላሾቹ የክፍልም ሆነ የቤት ስራ መስራት ስለማልወድ 55(45.83%)፣ድርሰትመፃፍስለሚከብደኝ 47(39.17%)፣ስርቼ ብመጣም የማገኘው ጥቅም ስለሌለ 6(5%) እና መምህሩ የሚሰጧቸውን መልመጃዎች ስለማያርሙ 12(10%) በማለት መልሰዋል። ከዚህ መጠይቅ ምላሽ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ሁለት አሉታዊ ምላሾች ስናይ የክፍልም ሆነ የቤት ስራ መስራት ስለማልወድ የሚለው ምላሽ ብንወስድ ብዙ ጥርጣሬ ውስጥ ሳንገባ ምላሹ ስለሚከብደኝ የሚለውን ጥቆማ እናገኛለን።ለምን ከበደ ብለን ስንጠይቅ ደግሞ የሚኖረው መልስ የክፍልም ሆነ የቤት ስራ መስራት ስለማልወድ ነው ስለዚህ ሁለቱም በአሉታዊነታቸው ተደጋጋፊ ናቸው።

**ሰንጠረዥ 20፡ መምህራችሁየድርሰትመልመጃዎችሲያርሙበአብዛኛውየትኛውንስልትይጠቀማሉ**

| መምህራችሁየድርሰትመልመጃዎችሲያርሙበአብዛኛውየትኛውንስልት ይጠቀማሉ | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| ሀ/ በስራችሁትየድርሰትመልመጃ ላይ ምልክት በማድረግ | 36 | 30.0 |
| ለ/ በሰራችሁትመልመጃውስጥ ስህተቶችን በመጻፍ | 10 | 8.33 |
| ሐ/ የተወሰኑደብተሮችንከታዩበኋላትክክለኛውንመልስበመንገር | 66 | 55.0 |
| መ/እጃችሁንእያወጣችሁእንድታነቡበማድረግናየተሳሳታችሁት ንበቀጥታበመንገር | 8 | 6.67 |
| ድምር | 120 | 100.0 |

የዘህ መጠይቅ ዓላማ መምህራን የድርሰት መልመጃዎችን ለማረም የሚጠቀሙትን ስልት ለማወቅ ነበር፤ጥያቄውን ተማሪዎቹ እንደሚከተለው መልሰዋል።በሰራችሁት የድርሰት መልመጃ ላይ ምልክት በማድረግ 36(30%)፣በሰራችሁት መልመጃ ውስጥ ስህተቶችን በመጻፍ10(8.33%)፣የተወሰኑ ደብተሮችን ከታየ በኋላ ትክክለኛውን መልስ በመንገር 66(55%) እና እጃችሁን እያወጣችሁ እንድታነቡ በማድረግ እና የተሳሳታችሁትን በቀጥታ በመንገር 8(6.67%) ተጠኝዎች መልሰዋል።የዘህ መጠይቅ ከፍተኛ ቁጥር የያዙት የተወሰኑ ደብተሮች ከታዩ በኋላ ትክክለኛውን መልስ በመንገር ያሉት ከግማሽ በላይ የሆኑ 66(55%) ተጠኚ ተማሪዎች ናቸው።ትኩረትም የምናደርገው በዚሁ ምላሽ ላይ ነው። ስለዚህ በሰራችሁት የድርሰት መልመጃ ላይ ምልክት በማድረግ ከመለው የተወሰነ ባሕሪይ ስለመወስድ ዞሮ ዞሮ ስልት ብለን ከምላሹ የምንወስደው ደብተር ይታያል መልስም ይነገራል የሚለውን ነው።

**ሰንጠረዥ 21፡ መምህራችሁ በጽሁፍ የሰራችሁትን መልመጃ ብትሳሳት የሚሰጡህ/ሽ/ ምላሽ ምን ይመስላል?**

| መምህራችሁበጽሁፍየሰራችሁትንመልመጃብትሳሳትየሚሰጡህ/ሽ/ ምላሽምንይመስላል? | ድግግሞሽ | መቶኛ |
|---|---|---|
| ሀ/ስህተትመስራቴእጅግያስቆጣቸዋል | 13 | 10.83 |
| ለ/ስህተትመስራቴንእንደስህተትወስደውየተሳሳትኩትን | 12 | 10.0 |
| ሐ/ /የሰረሰሁትንስህተትበማስተጋባት | 9 | 7.5 |
| መ/ስህተትመስራቴምንችግርእንደሌለውናወደፊትየማስተካከልበትንመንገድያሳዩኛል | 18 | 15 |
| ሠ/ ምንምአይነትአስተያየትሳይሰጡኝያልፉታል | 68 | 56.67 |
| ድምር የሚሰራ | 120 | 100.0 |

የዚህ መጠይቅ ዓላማ መምህራን ተማሪዎች በጽሁፍ የሰሩትን መልመጃ ቢሳሳቱ የሚሰጡትን ምላሽ ለመረዳት ነው፡፡የተጠኘዎቹ ምላሽ ስህተት መስራቴ እጅግ ያስቆጣቸዋል 13 (10.83%)፣ ስህተት መስራቴን እንደስህተት ወስደው የተሳሳትኩትን 12(10%)፣ የሰረሰሁትን ስህተት በማስተጋባት 9(7.5%)፣ስህተትመስራቴ ምን ችግር እንደሌለውና ወደፊት የማስተካከልበትን መንገድ ያሳዩኛል 18(15%) ምንም አይነት አስተያየት ሳይሰጡኝ ያልፉታል 68(15%) ተማሪዎች መልሰዋል፡፡ስለዚህ ተማሪዎቹ ቢሳሳቱ መምህሩ የሚሰጡት ምላሽ በአብዛኛዎቹ ተማሪዎች የተመረጠው ምንም አይነት አስተያየት ሳይሰጡኝ ያልፉታል ያሉት የ68ቱ(56.67% )ተማሪዎች ምላሽ ይሆናል፡፡

ሠንጠረዥ 22 ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸውን ፍላጎት ለማወቅ የተጠየቀ የመመዘኛ ጥያቄ ነው፡፡

| | በጣምከ ፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. የአማርኛቋንቋለመማርያለሽፍላጎት | 0.0% | 0.0% | 10.0% | 45.0% | 45.0% |
| 2.ወላጆችህ/ሽ/ለአማርኛቋንቋተናጋሪማ ህበረሰብእናለቋንቋውያላቸውበጎአመ ለካከት | 0.0% | 0.0% | 25.0% | 50.0% | 25.0% |
| 6.በትምህርትሂደትየአማርኛ ቋንቋ ጥያቄ ለመጠየቅ እና መልስ በመስጠት ሂደት የሚታደርገው/ጊው/ ተሳትፎ | 0.0% | 0.0% | 25.0% | 40.0% | 35.0% |
| 7.የክፍልምሆነየቤትስራዎችለመስራትየ ምታደርገው /የሚታደርጊው/ ጥረት | 0.0% | 0.0% | 10.0% | 50.0% | 40.0% |
| 8.ከጽሁፍ፣ከመጽሔት፣ከሬዲዮ፣ከጋዜ ጦች/ያገኘሄውን/ያገኘሽው/አዳዲስቃ ላትናአባባሎችበጽሑፍለመጠቀምየ ምታደርገው/የምታደርጊው /ጥረት | 0.0% | 5.0% | 20.0% | 25.0% | 50.0% |

የመጠይቅ 16 ዓላማ ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋን ለመማር ያላቸውን ፍላጎት ለማወቅ የተጠየቀ የመመዘኛ ጥያቄ ነው፡፡በመሆኑም የመጀሪያውን ጥያቄ ብናይ የአማርኛ ቋንቋ ለመማር ያለቸውን ፍላጎት የሚጠይቅ ሲሆን ምላሻቸው መካከለኛ10.0%፣ዝቅተኛ 45.0%፣በጣም ዝቅተኛ 45.0%፣ቀሪዎቹ ከፍተኛ እና በጣም ከፍተኛ ባዶ በመሆን ተመልሷል፡፡ ከምላሹ የምንረዳው የአብዛኛዎቹ ተማሪዎች ምላሽ አሉታዊ በመሆኑ የመማር ፍላጎት እንደሌላቸው ያመለክታል፡፡

2ኛውንመጠይቅ ስናይ የተማሪዎቹ ወላጆች ለአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ እና ለቋንቋው ያላቸው በጎ አመለካከት ምን እንደሆነ ለማወቅ ነው፡፡አላማው ወላጆች ለአማርኛ ቋንቋ እና ለተናጋሪው ህብረተሰብ በጎ(አዎንታዊ) አመለካከት ካላቸው

ልጆቹም(ተማሪዎቹም)በተወሰነ ደረጃ ለትምህርቱ ተነሳሽነት ይኖራቸዋል፡፡የወላጆቹ አመለካከት አሉታዊ ከሆነ በተወሰነ ደረጃ ተማሪዎቹ ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ ነው የሚሆነው፤በመሆኑም የተማሪዎቹን ምላሽ ስናይ መካከለኛ25.0%፣ዝቅተኛ 50.0%፣በጣም ዝቅተኛ 25.0%፣ቀሪዎቹ ከፍተኛ እና በጣም ከፍተኛ ባዶ በመሆን ተመልሷል ስለዚህ ምላሹ የሚያመለክተን አሉታዊ በመሆኑ በተማሪዎቹ ትምህርት ላይ ተጽእኖ ስለሚኖረው ድረሰት ሲጽፉ ለስህተቱ መንስዔ ባይሆንም ለምክንያቱ ግን የተወሰነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ፡፡

መጠይቅ 6፡በትምህርት ሂደት ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ጥያቄ ለመጠየቅ እና መልስ ለመስጠት የሚያደርጉትን ተሳትፎ ለመገንዘብ የቀረበ ነው፡፡አላማው ቀደም ሲል በሌላ መጠይቅ ቋንቋውን ለመማር ያላቸውን ፍላጎት ለማወቅ የተጠየቁት ጥያቄዎች ነበሩ፤ይሄኛው የዛኛውን ጥያቄ ምላሽ ማረጋገጫ ወይም ድጋፍ የሚሆን ምላሽ ምን እንደሚሆን ለማወቅ የቀረበ ነው፡፡በመሆኑም የተማሪዎቹን ምላሽ ስንመለከት መካከለኛ25.0%፣ዝቅተኛ 40.0%፣በጣም ዝቅተኛ 35.0%፣ቀሪዎቹ ከፍተኛ እና በጣም ከፍተኛ ምንም ሆኖ ተመልሷል፡፡ይህ ምላሽ የሚያስረዳን ተማሪዎቹ ጥያቄና መልስ ለማድረግ ፍላጎት እንደሌላቸው ነው የሚያመለክተው፡፡ይህ ማለት ደግሞ ለመማርም ፍላጎት እንደሌላቸው በሌላ መጠይቅ ስለመለሱ የላይኛውን መጠይቅ እውነት ያደርገዋል፡፡

መጠይቅ 7፡ የክፍልም ሆነ የቤት ስራዎች ለመስራት ተማሪዎች የሚያደርጉትን ጥረት ለማረጋገጥ የቀረበ ነው፡፡ ኣላማው በምርጫ መጠይቅ የቤት ስራ ትሰራላችሁን ተብሎ ለተጠየቀው መጠይቅ በተዘዋዋሪ እንደሚሰሩ እና እንደማይሰሩ ለማረጋገጥ የቀረበ ነው፡፡ በመሆኑም ምላሻቸውን ስናይ መካከለኛ10.0%፣ዝቅተኛ 50.0%፣በጣም ዝቅተኛ 40.0%፣ ቀሪዎቹ ከፍተኛ እና በጣም ከፍተኛ ምላሽ እንዳልተሰጣቸው ተመልክተናል፡፡ የአብዛኛዎቹ ተማሪዎች ምላሽ አሉታዊ በመሆኑ የክፍልም ሆነ የቤት ስራዎች ለመስራት ተማሪዎች የሚያደርጉትን ጥረት እንደሌለ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሚያመለክተን በአመራጭ መጠይቅ ላይ የቤት ስራ እንደማይሰሩ ለገለጹትን ማረጋገጫ ይሆናል፡፡

መጠይቅ 8፡ ከጽሁፍ፣ ከመጽሔት፣ ከሬዲዮ፣ ከጋዜጦች ያገኙትን አዳዲስ ቃላትና አባባሎች በጽሑፍ ለመጠቀም የሚያደርጉትን ጥረት ለማወቅ ነው፡፡ ሆኖም የመጠይቁ አላማ ለጽህፈት ትምህርት የሚሰጡትን ትኩረት ለማወቅ እና ተጨማሪ ነገር እንደሚጽፉ ለማረጋገጥ ነበር፡፡ ሆኖም ግን የተማሪዎች ምላሽ የሚያመለክተን አሉታዊ ምላሽ እንደሆነ ነው፡፡ ስንተነት ነው መካከለኛ20.0%፣ዝቅተኛ 25.0%፣በጣም ዝቅተኛ 50.0%፣ቀሪዎቹ ከፍተኛ 5እና በጣም ከፍተኛ ባዶ የሆነ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ስለዚህ ከጽሁፍ፣ ከመጽሔት፣

ከሬዲዮ፣ ከጋዜጦች ያገኙትን አዳዲስ ቃላትና አባባሎች በጽሑፍ ለመጠቀም የሚያደርጉት ጥረት እንደሌለ እንገነዘባለን፡፡

**ሠንጠረዥ 23 መምህራን የአማርኛ ቋንቋ ለማስተማር ያላቸው ፍላጎትን(ተነሳሽነትን)ለመገንዘብ የቀረበ የመመዘኛ ጥያቄ ነው፡፡**

| | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 5.የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ/ ቋንቋውንለማስተማር የሚጠቀሙበት ዘዴ ሳቢነት | 2.0% | 6.0% | 11.0% | 38% | 43% |

መጠይቅ 5፡ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቋንቋውን ለማስተማር የሚጠቀሙበት ዘዴ ሳቢነት እንዳለው ለመፈተሽ ነበር፡፡ ምላሻቸውን ስናይበጣም ከፍተኛ 2.0% ከፍተኛ6.0% መካከለኛ 11.0%፣ ዝቅተኛ 38.0% እና በጣም ዝቅተኛ 43.0% መርጠዋል፡፡ የተማሪዎቹ ምላሽ የሚያመለክተን የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቋንቋውን ለማስተማር የሚጠቀሙበት ዘዴ ሳቢነት እንደሌለው ነው፡፡ የመማር ማስተማሩ ሂደት ሳቢነት ከሌለው የስህተት ምንጭ ባይሆንም ለስህተት አፈጻጸሙ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5.ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳብ

### 5.1.ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ዋና አላማ አድርጎ የተነሳው በሲዳማ ክልል በሀዋሳ ከተማ አዳሬ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አፋቸውን በሲዳምኛ ቋንቋ የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ሰዋስዋዊ ስህተቶች መለየት ነው፡፡ ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ የሚከተሉት የትኩረት ጥያቄዎች በሲዳምኛ ቋንቋ አፍ ፈት የሆኑ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ሰዋስዋዊ ስህተቶች ዓይነቶች ምንምን ናቸው? ተጠኚዎቹ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ደርሰት ሲጽፉ ከሚፈጽሟቸው ሰውስዋዊ ስህተቶች ውስጥ የትኛው ስህተት በብዛት ተደጋግሟል? ለሰዋስዋዊ ስህተቶቹ መከሰት ምንጭ ወይም ምክንያት ምን ይሆን? ለሚሉት ምላሽ ለማግኘት በታላሚ ተማሪዎች በተጻፉ ድርሰቶች እና የጽሁፍ መጠይቆች እንዲሁም ከአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር በተደረጉ የቃለ-መጠይቅ ምልልሶች መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል፡፡

በድርሰቶቹ ውስጥ የተስተዋሉ አጠቃላይ የስህተቶች ዓይነቶች እና ብዛት የተቆጠሩት በሁለት ዙር በተጻፉት 240 ድርሰቶች ውስጥ ነው፡፡በነኚህ ድርሰቶች ውስጥ የተጻፉት ቃላት ብዛት 22272 ሲሆኑ በነኚህ ቃላት ውስጥ የተገኙት የስህተት ብዛቶች በቁጥር7996 በመቶኛ 36 ናቸው፡፡ታላሚ ተማሪዎች ሁለቱን ድርሰት ለመጻፍ የተጠቀሙባቸው ቃላት ብዛት በአማካይ 92.8 ሲሆን በአንድ ድርሰት በአማካይ የተገኘው ስህተት 33.32 እና የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 36 ነው፡፡ በጥናቱ የታዩ መሠረታዊ የስህተት ዓይነቶቹ የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች፣ የቋንቋ አወቃቀር ስህተቶቸ እና ምድብ የሌላቸው ስህተቶች እንደሚከተለው በዋናነት ተለይተዋል፡፡

በሁለቱም ዙር ከተጻፉት ድርሰቶች አብላጫውን የስህተት ዓይነት የያዘው የቋንቋ አጠቃቀም ምድብ ነው፤በአጠቃላይ ከተቆጠሩት እና ከተለዩት 7996 ስህተቶች ውስጥ 3997ቱ (36.05%)በዚህ ምድብ የተለዩ ናቸው፡፡ በአንድ ድርሰት ውስጥ የተከሰቱት አማካ ስህተተቶች 33.7ሲሆኑ አማካይ የስህተት ድግግሞሹ 36.43 ናቸው፡፡ከቋንቋ አጠቃቀም በመቀጠል ከፍተኛ የስህተት መጠን የተለየው የቋንቋ አወቃቀር ስህተት ነው፡፡የኸውም ከአጠቃላይ ስህተቶች 7996 ውስጥ 3800 (34.25%) የተሸፈነው በዚሁ የምድብ ስህተቶች ነው፡፡ በአንድ ድርሰት ውስጥ የተገኙት አማካይ ስህተቶች 35.11 ሲሆኑ አማካይ የስህተት ድግግሞሹ 38.16 ሆኗል፡፡ በመጨረሻም የተቆጠሩት በዓይነት ለመመደብ ወይም ለመለየት ያልተቻሉ የስህተት ክፍሎች ሲሆኑ ከአጠቃላይ ስህተት 199(1.8%) ስህተቶች

ተለይተዋል፤ በዚህ ምድብ በአንድ ድርሰት ውስጥ የተከሰቱት አማካይ ስህተቶች 1.68 ሲሆኑ የስህተት ድግግሞሹ 1.82 መሆኑ ተረጋግጧል፡፡በተሰበሰቡት መረጃዎች ለሰዋስዋዊ ስህተቱ መንስዔ የሆኑት በመረጃዎቹ ትንታኔ መሠረት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንደሆነ ከአናባቢ እና ተናባቢ ሆሄያት(ድምጾች) ልዩነት መሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል፤በተጨማሪ ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ መማር ሲጀምሩ ገና ከጅምሩ ሆሄያትን (ድምጾችን) ከቅርጻቸው እና ከይዘታቸው አንጻር ብቻ ሳይሆን የቃላትን አቀነጻጀቶችን ገና ከጅምሩ ለይተው ባለማወቃቸው እና የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መዋቅራዊ ሥርዓት ጭምር በጽህፈት ጊዜ ለስህተት የዳረጋቸው መሆኑ ተደርሶበታል፡፡

## 5.2.የመፍትሄ ሀሳብ

በማጠቃለያ ላይ እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሲዳማ ክልል በሀዋሳ ከተማ አዳሬ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አፋቸውን በሲዳምኛ ቋንቋ የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ሰዋስዋዊ ስህተቶች መለየት ነው፡፡ ይህን አላማ መሠረት በማድረግ በሲዳምኛ ቋንቋ አፍ ፈት የሆኑ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ሰዋስዋዊ ስህተቶች ዓይነቶች ፣የትኛው ስህተት በብዛት ተደጋግሟል፣ የሰዋስዋዊ ስህተቶቹ መከሰት ምንጭ ወይም ምክንያት ለማግኘት በታላሚ ተማሪዎች በተጻፉ ድርሰቶች እና የጽሁፍ መጠይቆች እንዲሁም ከአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር በተደረጉ የቃለመጠይቅ ምልልሶች መረጃዎች በመሰብሰብ መልሶች ተገኝተዋል፡፡ በመሆኑም ከጥናቱ ውጤት በመነሳት እና የማጠቃለያን ሀሳብ በማገናኘት የመፍትሄ ሀሳቡ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ለሰዋስዋዊ ስህተቱ መንስዔ የሆኑት በመረጃዎቹ ትንታኔ መሠረት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንደሆነ ፣የሲዳምኛ እና የአማርኛ ቋንቋ አናባቢ እና ተናባቢ ሆሄያት(ድምጾች) ልዩነት እና የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሥርዓተ-ጽህፈት ወይም መዋቅራዊ ህግ ጭምር መሆኑ ተደርሶበታል፤እነዚህን ችግሮች (ስህተቶች)ከነመንስዔያቸው ለማስወገድ

1.በአፍመፍቻ ቋንቋቸው እና በአማርኛ ቋንቋ መካከል ያለውን የአናባቢ እና ተናባቢ ድምጾች (ሆሄዎች መካከል)ያለውን ልዩነት ከዝቅተኛ ክፍል ጀምሮ ቢለማመዱ፣

2.በሲዳሚኛ እና በአማርኛ ቋንቋ መካከል ያለውን የመዋቅር ህጎችን ተማሪዎቹ እንዲለዩ ትኩረት ሰጥቶ ቢሠራ፣

3.የመማር ማስተማሩ ሂደት፣ የማስተማሪያ ግብዓቶች፣ማህበራዊ እና ሥነልቦናዊ ሁኔታዎች በቀጥታ የስህተት ምንጭ ወይም መንስዔ ባይሆኑም ለአፈጻጸሙ መንገድ ከፍተዋል፤ስለሆነም አጽንኦት ተሰጥቶ ቢሰራባቸው፣ እነኚህ አስተያየቶች በስራ ላይ ከዋሉ (ከተፈጸሙ) ሙሉ ቡሙሉ ባይሆን እንኳ መሻሻሎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

# ዋቢ ጽሁፎች


ልዑልሰገድ አሰፋ (1997)፡፡“በወላይትኛና ሲዳምኛ ተናጋሪዎች በአማርኛ ድርሰት ውስጥ የታዩ ስህተቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና፡፡”ለሁለተኛ ዲግሪ ሚሚያ የቀረበ ጥናት፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

መሠረት ጣፋ (2003)፡፡“በሀረማያና አዴሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋናዋና ስህተት አይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና፡፡”ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፣አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ( ያልታተመ)፡፡

ሙልጌታ አብስር (2003)፡፡በአርባምንጭ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት  ክፍል አፋቸውን በጋሞኛ ቋንቋ የፈቱ የሁለተኛ ዓመት የክላስተር ዕጩ መምህራን ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና፡፡” (ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፣አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ (ያልታተመ) ፡፡

ምህረት ሳዳሞ (1998)፡፡“በዋቻሞ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሀድይኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፍ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና፡፡”(ለሁለተኛ ዲግር ማሚያ የቀረበ ጥናት ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ( ያልታተመ)፡፡

ባየ ይማም (2000)፡፡የአማርኛ ሰዋስው፡፡አዲስ አበባ የተሸሻለ ሁለተኛ እትም፣እሌኒ ማተሚያ ቤት፡፡

ባየ ይማም (2003)፡፡ <u>አጭርና ቀላል</u> የአማርኛ ሰዋስው፡፡አዲስአበባ፣አልፋ ማተሚያ ቤት፡፡

ተስፋዬሸዋዬ (1986)፡፡ <u>አንብቦ የመረዳት</u> እና የመጻፍ ችሎታን ማዳበር፡፡አዲስአበባ፣ት.መ.. ማ.ማ.ድ ፡፡

ተክሌ አስፋው (1989)፡፡“በቡታጅራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አፋቸውን በመስቃንኛ ቋንቋ የፈቱ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶችትንተና፡፡” ለሁለተኛ  ዲግር ማሚያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ(ያልታተመ)፡፡

ተገኝ አህመድ (2000)፡፡ “አፋቸውን በከፍኛ ቋንቋ የፈቱ የቦንጋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሰልጣኝ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፍ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና፡፡” ለሁለተኛ ዲግር ማሟያ የቀረበ ጥናት ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ( ያልታተመ)፡፡

ያምላክሥራ ሕይወት (2008)፡፡“የአማርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ጽሑፍ ላይ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጭ ትንተና በአዲስ አበባ ከተማ ተተኳሪነት፡፡”ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ (ያልታተመ)፡፡

ያለው እንዳወቅ (2009)፡፡ የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር ፡፡አዲስ አበባ ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ዐብይ አሰፋ (1997)፡፡“አዲስ ከተማ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በደብረ ኃይለ ቅዱስ ራጉኤል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና፡፡” አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ፣ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

ደብሬ ተሰማ (1990)፡፡ “በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና የስህተት ምንጮች፡፡”አዲስአበባ ዩንቨርሲቲ፣ለሁለተኛ ድጊሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

ጌታሁን አማረ (1990)፡፡ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ ፡፡አዲስአበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት ፡፡

ጌታቸው እንዳላማው (2011)፡፡የቋንቋና ሥነልሳን መግቢያ፡፡አዲስ አበባ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡

Brown, H. (1994). Principles of Language Learning ad Teaching. New Jersey: Prentice Hall.

Byme (1997). Teaching writing skills. London: Longman group Ltd.

Byrne, D. (1988). Teaching Writing Skills.London: Longman.Flower, L. S. Teaching Writing Skills. Hong Kong: Longman Group Ltd.

Corder, S.P.(1967).”The Significance of Learners’ Error”IRAL.Vol.4,1-4;161-169 Crystal.

Dulay et.al.(1982).Language Two. Oxford: Oxford University

Ellis, R.(1989).Understanding Second Language Acquisition. 5thed Oxford: Oxford University Press.

Ellis, R. (2009). “Corrective Feedback and Teacher Development.”*L2 Journal.* Chang Jiang Scholar of Shanghai International Studies and University of Auckland, UCC on sortium for Language Learning and Teaching, UC Davis :http://escholarship.org/uc/item/2504d6w3 1(1).

Heaton, JB. (1991). *Writing English Language Test*. New York : Edinburg Gate.

Kavaliauskiene, G. (2009). Role of the mother tongue in learning. *English for specific purposes world*. 1(8).

Littlewood, W.(1984).Foreign and Second Language Learning. Cambridge: Cambridge University Press.

Norrish H, J. (1983).Language Learners and Their Errors. London and Basingstoke. McMillan Publishers Ltd.

Norish, J.(1992). Language Learners and their Errors. London: Macmillan Publishers Ltd.

Park, T.(2004). ‘’An Overview of Portifolio-based Writing Assessment.’’ *Columbia* University Working *Papers in TESOL & Applied Linguistics,*4(2),1-3.

Raymis, A. (1983).Techniques in the Teaching writing. New York: OUP.

Richards,J.C.(1971). ‹‹ A non-contrastive approach to Error Analysis> English

LanguageTeachingJournal,25,204-219.


Tangerpermpoon, T. (2009).Integrated approaches to improve students writing skill for Englishmajor students.*ABAC Journal, 28* (2),1-9.

Ur,P.(1996). A course in language Teaching Practuse and theory. Cambridge: Cambridge University Press.


White, R.(1980).Teaching Written English. Great Britain: J.W. Arrow smith Ltd, Bristol.

# አባሪዎች


# አባሪ አንድ




# አባሪ ሁለት




# አባሪ ሶስት




## አባሪ አራት




# አባሪ አምስት



## አባሪ ስድስት



## አባሪ ሰባት



አባሪ 8

ለመምህራን የተዘጋጁ የቃል መጠይቅ ጥያቄዎች

ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ስለሆኑ አመሰግናለሁ፡፡

1.እርስዎ የጽህፈት መልመጃዎችን ሲያርሙ በአብዛኛው ተማሪዎች የሚፈጽሟቸው የስህተት አይነቶ የትኞቹ ናቸው?

2.እርስዎ ተማሪዎች በጽሁፍ ሀሳባቸውን ሲገልፁ ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች መንስኤ ናቸው ብለው የሚገምቷቸውን ምክንያት ዘርዝሯቸው

3.በሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ የቀረበው ትምህርት የተማሪዎችን ችሎታና ፍላጎት ይመጥናል? እንዴት

4.በአማርኛ ቋንቋ ትምህር የጽህፈት ት/ት አስመልክቶ ሎትን አስተያየት ቢገለፁልን፡፡

ለቃለ መጠይቁ ስለተባበሩኝ አመሰግናለሁ፡፡

በአዳሬ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተዘጋጀ ቃለመጠይቅ

የቃለ-መጠይቁ ምላሾች ቅጂ

ከአራት መምህራን ጋር የተደረገ ምልልስ

ሰኔ 02/10/2015

አዳሬ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

ሰዓት ከ5.00 እስከ 5.30

ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ የግል ትውውቅ ካደረግን በኋላ የጥናቱ ዓላማ በሲዳምኛ አፍ ፈት የሆኑ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ለመተንተን እንደሆነ ነግሬ ቃለመጠይቁም የተዘጋጀው ይህንኑ መሠረት በማድረግ እንደሆነ በመግለጽ ወደ ቃለምልልሱ ገባን።

ጥያቄ1፡.እርስዎ የጽህፈት መልመጃዎችን ሲያርሙ በአብዛኛው ተማሪዎች የሚፈጽሟቸው የስህተት አይነቶች የትኞቹ ናቸው?

መምህር 1፡‹‹ፊደላትን በተለይ ሳልስና ሳድስን ለይቶ አለመጠቀም ነው የሚታየኝ።››

መምህር2፡‹‹እንደሚናገሩትም ስለሚጽፉ በአብዛኛው የሲዳምኛ አጠቃቀም ራብእ እና ሀምስ ግእዙን ፊደል እየለወጡ ስለሚጠቀሙ የሚታየውም የግእዝ ፊደል አጻጻፍ ነው።››

መምህር 3፡‹‹የአማርኛን ቃላት አስተካክለው ያለመጻፍ ስህተት ይታያል።››

መምህር 4፡‹‹የአማርኛን ፊደሎች አስታካክለው አይጽፉም በተለይ የመጀመሪያ ረድፍ ፊደሎችን አይጽፉዋቸውም።..››

ጥያቄ2፡ እርስዎ ተማሪዎች በጽሁፍ ሀሳባቸውን ሲገልፁ ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች መንስኤ ናቸው ብለው የ ሚገምቷቸውን ምክንያት ዘርዝሯቸው

መምህር 1፡‹‹በሲዳሚኛ ቋንቋ የሌሉትን የአማርኛ ፊደላት መጻፍ ስለማይችሉ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተጽእኖ ሳያደርግ አይቀርም››

መምህር 2፡ ‹‹የሚጽፉት አማርኛውን እንደሚናገሩት ስለሆነ የሲዳምኛ ቋንቋ ተጽእኖ ሳያደርግባቸው አይቀርም።››

መምህር 3፡ ‹‹አማርኛ ሲናገሩ ግእዙን ፊደል ስለማይጠሩ የሲዳምኛ ቋንቋ ችግር ሳይሆን አይቀርም››

መምህርት 4፡ሲዳሚኛ ኩሽቲክ ነው አማርኛ ሴሜቲክ ነው ስለዚህ የኩሽቲክ ተናጋሪዎች የሴም ፊደላቶችን አንዳንዶችን በትክል መጥራት አይችሉም፡፡››

ጥያቄ፡ 3፡.በሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ የቀረበው ትምህርት የተማሪዎችን ችሎታና ፍላጎት ይመጥናል?እንዴት

መምህር፡ 1፡‹‹አይመጥንም ምክንያቱም የሲዳማ ተማሪዎችን ዳራ ያገናዘበ አይደለም ፡፡››

መምህር፡2፡‹‹ አይመጥንም፤ምክንያቱም የሲዳማ 9ኛ ክፍል ተማሪዎች አፋቸውን የፈቱት በሲዳሚኛ፣ከታች(በዝቅተኛ) ክፍልም እየተማሩ የመጡት ሲዳምኛን ትኩረታቸውም በሲዳምኛ ላይ ስለሆነ ከተማሪው ቋንቋ እና ባህል አንጻር መጽሀፉ አልተዘጋጀም፡፡››

መምህር3፡‹‹አይመጥንም፤ምክንያቱም የሲዳማን ባሕል፣የተማሪውን ሁኔታ እና አካባቢ ያልተመለከተ ስለሆነ ትኩረት ሰጥተው አይማሩም፡፡››

መምህርት4፡አይመጥንም፤ የተማሪውን አካባቢ፣አኗኗር እና ቋንቋውን ሳያገናዝብ የታተመ መጽሀፍ ነው፡፡››

ጥያቄ 4፡. ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ ትምህር የጽህፈት ትምህርትን አስመልክቶ እንዴት ማሻሻል(መለማመድ) እንዳለባቸው አስተያየት ቢገለፁልን

መምህር1፡‹‹በአማርኛ እና በሲዳምኛ ፊደላት (ሆሄያት)መካከል ያለውን ልዩነቶች በ9ኛ ክፍል ሳይሆን ከዝቅተኛ ክፍል ጀምሮ እየለዩ እና እየተለማመዱ መምጣት አለባቸው፡፡››

መምህር 2፡ ‹‹ከፊደል ጀምሮ ቃላትን አረፍተ ነገርን እና ከዚያ በላይ ያሉትን የአማርኛውን የጽህፈት ሥርአት ከ5ኝ ክፍል ጀምሮ በትኩረት ማለማመድ ይገባል፡፡››

መምህር 3፡‹‹ተማሪዎቹ በአብዛኛው የሚቸገሩት በሣድስ እና ሣልስ እንዲሁም በሁለቱም ቋንቋ ያሉትን አናባቢዎች ለይቶ የመጻፍ ጉዳይ በመሆኑ በእነዚህ ላይ ከዝቅተኛ ክፍል ጀምሮ ቢሰራባቸው የተሸለ ይሆናል፡፡››

መምህርት 4፡‹‹ማስተማሪያ መጽሀፍ ሲዘጋጅ ባጭሩ የሲዳማ ተማሪዎችን ዳራ ያላገናዘበ በፌዴራል ደረጃ ቢሆንም አማርኛ 2ኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎችን ያለገናዘበ ስለሆነ

ለወደፊቱ የጋራ የሚያደርግ መጽሀፍ ቢዘጋጅ ለመማር ተነሳሽነት ይኖራል፡፡ሌላው የሲዳማ ተወላጆች በአብዛኛው የሚታወቁበት አማርኛ ሲናገሩም ሆነ ሲጽፉ በአማርኛ ግእዝና ሳድስ ቦታ ራብእንና ሀምስን ሲጠቀሙ ነው ይህንን ለማስተካከል ትኩረት ሰጥቶ ቢሰራ መሻሻል ይኖራል ብዬ አስባለሁ፡፡

አባሪ10

**አዲስአበባዩኒቨርስቲ**

**የኢትዮጵያቋንቋዎችናስነ-ጽሁፍ ት/ትክፍል**

**በተማሪዎችየሚሞላመጠይቅ**

**ውድተማሪዎች**

የዚህ መጠይቅ ዓላማ አፋቸውን በሲዳመኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ላይ መፍትሔዎችን ለሚጠቁመው ጥናት መረጃ መሰብሰብ ነው፡፡

ከጥናቱ የሚገኘው ውጤት ችግሮችን ለማስወገድ ካልቻለም ለማቃለል ዕገዛ የሚያደርጉ ሐሳቦን ለመሰንዘር እንዲያስችል ይታመናል፡፡ ጥናቱ ውጤታማ እንዲሆን ትክክለኛውን መረጃ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

ስለዚህ መጠይቁን በጥንቃቄ አንብባችሁ ተገቢውን መልስ እንድትሰጡ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

ማሳሰቢያ፡-

1. በመጠይቁ ላይ ስም ፣ቁጥርና ክፍል አይፃፍም

2.መጠይቁን በሌላ ሰው ማስሞላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባ አይፈቀድም

3.አጠገብ ካለተማሪ አይቶ መሙላት ፈፅሞ አይፈቀድም

## ክፍል አንድ

*መመሪያ*: ከዚህ በታች የቀረቡ ጥያቄዎች እያንዳንዳቸው አምስት አምስት አማራጭ መልሶ ይዘዋል። እያንዳንዱ በጥንቃቄ ካነበብክ/ሽ/በኋላ ለጥያቄው መልስ ይሆናል

ያልከውን/ያልሽውን/አንድመልስ ብቻመርጠህ/ሽ/ ከፊት ለፊት ያለው ፊደል ክበበው/ክበቢው/

1.በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ትገኛል/ሽ/

ሀ/ሁልጊዜ እገኛለሁ ለ/አብዛኛውን ጊዜ እገኛለ ሐ/በመጠኑእገኛለሁ

መ/አብዛኛውን ጊዜ አልገኝም ሠ/በፍፁም አልገኝም

2.በተራ ቁጥር አንድ ለቀረበው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ ከ ,ሔ, እስከ,ሠ, ካሉት አንዱ ከሆነ ምክንያቱ ምንድነው

ሀ/አማርኛ ቋንቋ መማር ስለማልወድ ለ/ከመምህሩ ጋር ስለማልስማማ ሐ/አማርኛን ባልማረውም ማወቅ ስለምችል

መ/የትምህርቱ አቀራረብ ስለማያስደስት ሠ/ትምህርቱ በጣም ስለሚከብደኝ

3.በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ አማርኛን የትምማሪው /የምትማሪው/

ሀ/ሙሉ በሙሉ ከመማሪያ መጽሐፉ ነው ለ/በአብዛኛው ከመማሪያ መጽሐፉ ነው

ሐ/በመጠኑ ከመማሪያ መጽሐፉ ነው መ/በአብዛኛው ከመማሪያ መጽሐፉ ውጪ ነው

ሠ/ሙሉ በሙሉ ከመማሪያ መጽሐፉ ውጪነው

4.ትምህርቱ በአብዛኛው የሚያተኩረው በየትኛው ይዘት ላይ ነው

ሀ/በአረፍተ ነገር አይነቶች አመሰራረትና አገነባብ ለ/ስለ ድምፆች አፈጣጠርና አገነባብ

ሐ/ስለቃላት አመሰራረት መ/ስለቃላት የተለያየ ፍቺ ሠ/ስለ ቋንቋ የተለያዩ አጠቃቀሞች

5.በአማርኛ ስትጽፍ/ፊ/በይበልጥ የሚያስቸግርህ/ሽ/ክፍል የትኛው ነው

ሀ/በቃላት ድምፆችን በተገቢው ፊደል ወክሎ መፃፍ ለ/መደብ አመልካች ቅጥያዎች በትክክል

ሐ/ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ ተጠቅሞ አለመጽሐፍ    መ/ሀሳብ በትክክል አቀናብሮ መፃፍ

6.አማርኛ መምህራችሁ ጽህፈትን ለማስተማር በመማሪያ መጽሀፉ ከቀረቡ መልመጃዎች በተጨማሪ ከመጽሐፍ፣ ከመጽሄት፣ ከጋዜጣች አንብባችሁ ወይም ሰዎችን ጠይቃችሁ የተረዳችሁትን ጽፋችሁ እንድትመጡ ያደርጋሉ፣

ሀ/ሁልጊዜ ያደርጋሉ    ለ/አብዛኛውን ጊዜ ያደርጋሉ   ሐ/በመጠኑ ያደርጋሉ

መ/በአዛኛውን ጊዜ አያደርጉም    ሠ/በፍፁም አድርገው አያውቁም

7.መምህራችሁ በትምህርት ቤታችሁ ለተቋቋሙ የስነ-ጽሁፍና ድራማ ወይም ሚኒሚዲያ ክበባት ስነጽሁፎች ወይም ዘገባዎችን እንድታቀርቡ ያበረቷቷቸኋል

ሀ/ዘወትር ያበረታታሉ    ለ/አብዛኛው ጊዜ ያበረታታሉ    ሐ/በመጠኑ ያበረታታሉ
መ/አልፎ አልፎ ያበረታታሉ    ሠ/በፍፁም ኤበረታቱም

8.መምሀራችሁ በጽሁፍ የሚመለስ የክፍል ወይም የቤት ስራ ይሰጧቸኋል

ሀ/ሁል ጊዜ ይሰጣሉ    ለ/አብዛኛውን ጊዜ ይሰጣሉ    ሐ/በመጠኑ ይሰጣሉ

መ/አብዛኛውን ጊዜ ይሰጣሉ    ሠ/በፍፁም አይሰጡንም

9.በመምህራችሁ የሚሰጧችሁ የጽሁፍ መልመጃዎች በአብዛኛው የሚያተኩሩት

ሀ/በቃላት አረፍተ ነገር መስራት    ለ/ደብዳቤ ወይም ዘገባ መፃፍ

ሐ/ረጅም ጽሁፍ ማሳጠር ወይም አጭ ጽሁፍ መሳጠር

መ/በተመረጡ ርዕሶች ላይ ልቦለዶችን ወይም ኢልቦለዶችን መፃፍ

10.መመሀራችሁ በክፍልም ሆነ በቤት የሚሰሩ የጽሁፍ /ድርሰት/መልመጃዎችን ያርማሉ

ሀ/ሁልጊዜ ያርማሉ    ለ/አብዛኛው ጊዜ ያርማሉ    ሐ/በመጠኑ ያርማሉ
መ/አልፎ አልፎ ያርማሉ    ሠ/በፍፁም አርመው አያውቁም
11.አንተ (አንቺ) ለክፍል ስራ ወይም ለቤት ስራ የሚሰጣችሁን የጽሁፍ /የድርስት/ መልመጃዎች ትሰራለህ/ሽ/
ሀ/ሁል ጊዜ እሰራለሁ    ለ/አብዛኛውን ጊዜ እሰራለሁ    ሐ/በመጠኑ እሰራለሁ
መ/አልፎ አልፎ እሰራለሁ    ሠ/ሰርቼ አላውቅም

12.በተራ ቁጥር አስራ አንድ ለቀረበው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ ከ ,ሐ, እስከ,መ, ካሉት አንዱ ከሆነ ምክንያቱ ምን ይመስልሃል/ሻል/ ሀ/የክፍልም ሆነ የቤት ስራ መስራት ስለማልወድ ለ/ድርሰት መፃፍ ስለሚከብደኝ ሐ/ሰርቼ ብመጣም የማገኘው ጥቅም ስለሌለ መ/መምህሩ የሚሰጧቸውን መልመጃዎች ስለማያርሙ

13.መምህራችሁ የድርሰት መልመጃዎች ሲያርሙ በአብዛኛው የትኛውን ስልት ይከተላሉ

ሀ/በስራችሁት የድርሰት መልመጃ ላይ ምልክት በማድረግ

ለ/በስራችሁት መልመጃ ውስጥ የታዩ ስህተቶችን በመጻፍ

ሐ/የተወሰኑ ደብተሮችን ካዩ በኋላ ትክክለኛውን መልስ በመንገር

መ/እጃችሁን እያወጣችሁ እንድታነቡ በማድረግና የተሳሳታችሁትን በቀጥታ በመንገር

14.መምህራችሁ በጽሁፍ የሰራችሁትን መልመጃ ብትሳሳት የሚሰጡህ/ሽ/ ምላሽ ምን ይመስላል

ሀ/ስህተት መስራቴ እጅግ ያስቆጣቸዋል

ለ/ስህተት መስራቴን እንደስህተት ወስደው የተሳሳትኩትን

ሐ/የሰረሰሁትን ስህተት በማስተጋባት

መ/ስህተት መስራቴ ምን ችግር እንደሌለውና ወደ ፊት የማስተካከልበትን መንገድ ያሳዩኛል ሠ/ምን አይነት አስተያየት ሳይሰጡኝ ያልፉታል

## ክፍልሁለት

መማሪያ፡ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥንቃቄ አንብበህ/ሽ/ ከጥያቄዎቹ ትይዩ ከቀረቡት መመዘኛዎች ውስጥ ትክክለኛ የሆነውን በመምረጥ በሳጥኑ ትይዩ ውስጥ የውስጥ ትክክለኛ የሆነውን በመምረጥ በሳጥኑ ትይዩ ውስት✓ምልክት በማድረግ አመልክት/ቺ/

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | መመዘኛዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣምከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣምዝቅተኛ |
| 1 | የአማርኛቋንቋለመማርያለሽፍላጎት | | | | | |
| 2 | ወላጆችህ/ሽ/ለአማርናቋንቋተናጋሪማህበረሰብናለቋንቋውያላቸውበጎአመለካከት | | | | | |
| 3 | ያደክበት /ሽ/አካባብአማርኛተናጋሪዎችጋርያለውልዩነት | | | | | |
| 4 | የአፍመፍቻቋንቋህ/ሽ/አማርኛቋንቋንእንደልብህ/ሽ/ እንዳትጠቀምያሳደረብ/ሽ/ ተጽዕኖ | | | | | |
| 5 | የአማርኛቋንቋመምህርህ/ሽ/ ቋንቋውንለማስተማርየሚጠቀሙበትዘዴሳቢነት | | | | | |
| 6 | በትምህርትህደትትጥያቄለመጠየቅናመልስበመስጠትሂደትየሚታደርገው/ጊው/ ተሳትፎ | | | | | |
| 7 | የክፍልምሆነየቤትስራዎችለመስራትየምታደርገው /የሚታደርጊው/ ጥረት | | | | | |
| 8 | ከጽሁፍ፣ከመጽሔት፣ከሬዲዮ፣ ከጋዜጦች/ያገኘሄውን/ያገኘሽው/ አዳዲስቃላትናአባባሎችበጽሑፍለመጠቀምየምታደርገው/የምታደርጊው /ጥረት | | | | | |

# ማረጋገጫ

በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር ተማሪ የሆንኩ መስከረም በየነ ‹‹በሲዳምኛ አፍ ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ሰዋስዋዊ ስህተቶች ትንተና በአዳሬ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት›› በሚል ርዕስ በድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ጥናት የእኔው ሥራ መሆኑን እየገለጽኩ ለሥራው የተጠቀምኩት ድርሳናት እና ዋቢዎች በሙሉ በትክክል መግለጼን በፊርማዩ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም መስከረም በየነ

ፊርማ----------------------

ቀን---------------------